# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( እ.ኤ.አ 1563)

## መግቢያ

### የጌታ ቀን ፡ 1

### 1. በሕይወትም ሆነ በሞት ውስጥ ብቸኛው መጽናኛህ ምንድነው?

ሀ) እኔ የራሴ አለመሆኔ፣ ነገር ግን ስጋየ እና ነፍሴ፣ በህይወትም ሆነ በሞት የታማኝ መድህኔ የኢየሱስ ክርስቶስ መሆኔ። ኃጢአቴን ሁሉ በክቡር ደሙ ከፍሎ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አውጥቶኛልና። በሰማያት ያለዉ አባቴ ሳይፈቅድ ከራሴ ጸጉር አንዲት እንኳን እስከማትወድቅ ድረስ ይጠብቀኛል፣ይልቁንም ነገር ሁሉ ለደህንነቴ በአንድነት ተባብሮ ይሰራል። ምክንያቱም እኔ የእርሱ ነኝና፣ ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስ የዘላለም ሕይዎት አረጋግጦልኛል፣ እንዲሁ በሙሉ ልቤ ከአሁን ጀምሮ ለእርሱ ለመኖር እንድፈቅድ እና ዝግጁ እንድሆን አድርጎኛል።

ሮሜ 14:7፣8፣ 1ኛ ቆሮ 6:19፣ 1ኛ ቆሮ 3:23፤ቲቶ 2:14፣ 1ኛ ጴጥ 1:18፣19፤1ኛ ዮሐ 1:7፤1ኛ ዮሐ 2:2፣12፣ ዕብ 2:14፤ 1ኛ ዮሐ 3:8፤ ዮሐንስ 8:34-36፣ ዮሐ 6:39; ዮሐ 10:28; 2ኛ ተሰ 3:3; 1ኛ ጴጥ 1:5፣ ማቴ 10:29-31፤ሉቃ 21:18፣ ሮሜ 8:28፣ 2ኛ ቆሮ 1:20-22፤ 2ኛ ቆሮ 5:5፤ ኤፌ 1:13፣14፤ ሮሜ 8:16፣ ሮሜ 8:14፤ 1ኛ ዮሐንስ 3:3

### 2. በዚህ የመጽናናት ደስታ ዉስጥ ሆነው ለመኖር እና ለመሞት ምን ማወቅ አለብዎት?

ሀ) ሶስት ነገሮች፡ አንደኛ፡- የእኔ ኃጢአት እና መከራ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ፤ሁለተኛ፡- ከኃጢያቴና ከመከራዬ ሁሉ እንዴት ነፃ እንደወጣሁ፤ ሦስተኛ፡- ለእንዲህ ያለው መዳን እግዚአብሔርን እንዴት ላመሰግነው እንዲገባኝ።

ማቴ 11:28-30፤ ሉቃ 24:46-48፤ 1ኛ ቆሮ 6:11፤ ቲቶ 3:3-7፣ዮሐ 9:41፤ዮሐ 15:22፣ ዮሐ 17:3፤ ሐዋ 4:12፤ ሐዋ 10:43፣ ኤፌ 5:8-11፤ 1ኛ ጴጥ 2:9፣ 10፤ ሮሜ 6:1፣2፣12፣13

# *የሃይደልበርግ ካቲኪዝም ( ኢ.ኤ.አ 1563)*

***ክፍል አንድ፡ መከራ***

**የጌታ ቀን ፡ 2**

***3. መከራህን ወደ ማወቅ እንዴት መጣህ?***

የእግዚአብሔር ህግ ነገረኝ።

ሮሜ. 3፡20 ፤ 7፡7-25

***4. የእግዚአብሔር ህግ ምን ይጠይቀናል?***

በማቴዎስ መጽሃፍ 22፡37-40 ክርስቶስ በጥቅሉ ይህንን ያስተምረናል፡-

❝አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።❞

❝ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።❞

❝ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።❞

❝በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።❞

ዘዳግም 6: 5፣ ሌዋ. 19፡18

***5 በዚህ ልክ መኖር ትችላለህን ?***

አይ አልችልም።

እግዚአብሔርን እና ባልንጀራየን የመጥላት ተፈጥሯዊ ዝንባሌ አለኝ።

# የሃይድልበርግ ካቲኪዝም( እ.ኤ.አ 1563)

ሮሜ.3፡9-20፣23 ፤1ኛ ዮሐ 1፡8፣10፣ ዘፍ. 6፡5 ፣ ኤር 17፡9 ፣ ሮሜ 7፡23-24 ፣ 8፡7 ኤፌ 2፡1-3 ፣ ቲቶ 3፡3

## *የጌታ ቀን ፡ 4*

*6. አምላክ ሰዎችን እንዲህ ክፉና ጠማማ አድርጎ ፈጥሯልን?*

ሀ) አልፈጠረኝም

ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን በእውነት እንዲያውቁ፣ በፍጹም ልባቸው እንዲወዱት፣ እግዚአብሔርንም እንዲያመሰግኑትና እንዲያከብሩት ፣ በዘላለም ደስታ እንዲኖሩ እግዚአብሔር መልካምና በራሱ አምሳል ማለትም በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና ፈጠራቸው።

ዘፍ 1፡31፣ ዘፍ 1፡26-27፣ ኤፌ 4፡24፣ ቆላ 3፡10፣ መዝ 8

*7. ታዲያ ይህ የተበከለ የሰዉ ልጅ ተፈጥሮ ከየት መጣ?*

የመጀመሪያ ወላጆቻችን የሆኑት የአዳም እና ሄዋን በገነት አለመታዘዝና ዉድቀት። ይህ ውድቀት ተፈጥሮአችንን ስለመረዘው እኛ ሁላችንም በኃጢአት ሁኔታ ተጸንሰን እንዲሁ ደግሞ ተወልደናል።

ዘፍ፡3፣ ሮሜ 5፡12፣18-19፣ መዝ 51፡5

**8. ለመሆኑ ታዲያ ምንም መልካም ነገር ማድረግ እስከማንችል ድረስ የተበላሸን እና ወደ ኃጢያት ሁሉ ያዘነበልን ነን?**

አዎ፣በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም ካልተወለድን በስተቀር።

ዘፍ 6፡5፣ 8፡21፣ ዕዮ 14፡4፣ ኢሳ 53፡6፣ ዮሐ 3፡3-5

## *የጌታ ቀን ፡ 4*

*9. በእዉኑ እግዚአብሔር በህጉ ማድረግ የማንችለውን በመጠየቅ ኢ-ፍታሃዊነት አላደረገብንምን?*

አይደለም፣እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ህግን መጠበቅ ከሚያስችል አቅም ጋር ፈጥሯቸዋልና።

ነገር ግን በሰይጣን አማካኝነት ተነሳስተው በፈቃድ ላይ በተመሰረተ አለመታዘዝ ራሳቸውን እና ከእነሱ የሚወለዱትን ሁሉ ይህንን ስጦታ ገፈፉ፡፡

ዘፍ 1፡31 ፣ ኤፌ 4፡24፣ ዘፍ 3፡13 ፣ ዮሐ 8፡44፣ ዘፍ 3፡6፣ ሮሜ 5፡12፣18፣19

***<u>10. እግዚአብሔር እንዲህ ያለዉን አለመታዘዝ እና ዓመጸ ሳይቀጣ ይተዋልን?</u>***

በፍጹም አይተዉም፡፡

እግዚአብሔር ይዘነው በምንወለደው ኃጢያት እንዲሁም በግል በምንሰራው ኃጢያት እጅግ ተቆጥቷል፡፡ እንደ ጻድቅ ዳኛ እግዚአብሔር ሀጢያቶቻችንን አሁን እንዲሁም ለዘለዓለም ይቀጣቸዋል እንዲህ ብሏልና፡-

"በሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ የማይጠብቅና የማይታዘዝ ሁሉ የተረገመ ነው፡፡"

ዘጸ 34፡7፣ መዝ 5፡4-6 ፣ናሆ 1፡2 ፣ ሮሜ 1፡18 ፣ኤፌ 5፡6 ፣ ዕብ 9፡27 ፣ ገላ 3፡10 ፣ ዘዳ 27፡16

***<u>11. እግዚአብሔር ግን መሐሪ አይደለምን?</u>***

በርግጥም እግዚአብሔር መሃሪ ነው፣ ነገር ግን ጻድቅም ጭምር፣ በሃያል ክብሩ ላይ የተደረገው ኃጢያት በሃያል ቅጣት ይኸውም በነብስ እና ስጋ የዘለዓለም ቅጣት ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ጽድቅ ይፈልጋል፡፡

ዘጸ 34፡6-7 ፣ መዝ 103፡88-9፣ ዘጸ 34፡7 ፣ ዘዳ 7፡9-11 ፣ መዝ 5፡4-6፣ ዕብ 10፡30-31፣ ማቴ 25፡35-46

# *የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)*

### *ክፍል ሁለት፡ ነጻ መዉጣት*

### *የጌታ ቀን ፡ 5*

***<u>12. እንደ እግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ ከሆነ አሁንም ሆነ ለዘለአለም ቅጣት ይገባናል፣ ታዲያ እንዴት ይህንን ቅጣት አምልጠን ወደ እግዚአብሔር ቸርነት መመለስ እንችላለን?</u>***

እግዚአብሔር የእሱ ፍትህ እንዲረካ ይፈልጋል፡፡ የእሱ ፍትህ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ በእኛ በራሳችን ወይም በሌላ አማካኝነት እንዲከፈልባቸው ይጠይቃል፡፡

ዘጸ፡ 23፡7፣ ሮሜ 2፡1-11፣ ኢሳ 53፡11 ፣ሮሜ 8፡3-4

***<u>13. እኛ ራሳችን ይህንን ዋጋ መክፈል እንችላለን?</u>***

በፍጹም አንችልም፡፡እንዲያዉም ዕዳችንን ቀን በቀን እንጨምረዋለን፡፡

ማቴ 6፡12 ፣ ሮሜ 2፡4-5

***<u>14. ከፍጥረት ሁሉ ሌላ ማንኛዉም ፍጡር አንድ እንኳ ቢሆን ይህንን ክፍያ ስለእኛ መፈጸም የሚቻለው አለ?</u>***

የለም፡፡ ሲጀመር እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጥፋት ሌላውን ፍጥረት አይቀጣም፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ተራ ፍጥረት እግዚአብሔር በኃጢያት ላይ ያለውን ዘለአለማዊ ቁጣ መሸከም እና ከዚያ ሌሎቹን ነጻ ማዉጣት አይችልም፡፡

ሕዝ፡ 18፡4፣20 ፣ ዕብ 2፡14-18፣ መዝ 49፡7-9 ፣ 130፡3

***<u>15. ታዲያ ምን አይነት መካከለኛ እና ነጻ የሚያወጣ ነው የሚያስፈልገን?</u>***

እዉነተኛ እና ጻድቅ ሰው፣ ነገር ግን ከሁሉም ፍጥረቶች በሃይል የሚበልጥ፣ እርሱም ደግሞ እዉነተኛ አምላክ የሆነ፡፡

ሮሜ 1፡3 ፣ 1ኛ ቆሮ 15፡21 ዕብ 2፡17፣ ኢሳ 53፡9 2ኛ ቆሮ 5፡21፣ ዕብ 7፡26፣ ኢሳ 7፡14 ፣ 9፡6 ኤር 23፡6 ዮሐ 1፡1

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

### የጌታ ቀን ፡ 6

**_16. መካከለኛው እውነተኛ እና ጻድቅ ሰው መሆን ያለበት ለምንድነው?_**

የእግዚአብሔር ፍትህ ኃጢያትን ያደረገው የሰው ልጅ ተፈጥሮ ለሰራው ኃጢያት እንዲከፍል ይጠይቃል፣ ነገር ግን ኃጢያተኛው የሰው ልጅ ይህንን ዕዳ ለሌሎች ሊከፍል ፈጽሞ አይቻለውም፤

ሮሜ 5፡12 ፣15 1ኛ ቆሮ 15፡21 ዕብ 214-16 ዕብ 7፡ 26-27 ፣ 1ጴጥ 3፡18

**_17. መካከለኛው እውነተኛ አምላክ መሆንስ ለምን አስፈለገው?_**

ምክንያቱም መካከለኛው በመለኮታዊ ሀይሉ የእግዚአብሔርን የቁጣ ክብደት በሰብዓዊነቱ መሸከም እንዲችል ከዛም ጽድቅ እና ህይወትን እንዲዋጅልን እና እንዲመልስልን።

ኢሳ 53 ፣ ዮሐ 3፡16 ፣ 2ኛ ቆሮ 5፡21

**_18. ይህ እውነተኛ አምላክ ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ እዉነተኛ እና ጻድቅ ሰው የሆነው መካከለኛ ማነው?_**

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ፣ እኛን ሙሉ በሙሉ ነጻ ሊያወጣን ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ሊያደርገን የተሰጠን።

ማቴ 1፡21-23 ፣ ሉቃ 2፡11 1ጢሞ 2፡5፣ 1ቆሮ 1፡30

**_19. ይህንን ወደማወቅ እንዴት መምጣት ትችላለህ/ሽ?_**

ሀ) ቅዱሱ ወንጌል ይህንን ይነግረኛል። እግዚአብሔር በገነት ያለውን ወንጌል አስቀድሞ መግለጥ ጀመሮ ነበር፤ ከዚያም በቅዱስ አባቶች እና በነቢያት እንዲታወጅ አደረገ፣ በህግ እና መስዋዕት ስርዓትም እንደጥላ ሆኖ እንዲታይ አድርጎ፣ ከዛም በመጨረሻ በተወደደው ብቸኛ ልጁ ሙሉ በሙሉ ፈጸመው።

ዘፍ 3፡15 ዘፍ 22፡18 ፣ 49፡10፣ ኢሳ 53 ኤር 23፡5-6 ሚካ 7፡18-20 ዘፍ 10፡43 ዕብ 1፡1-2 ሌዋ 1-7 ፣ ዮሐ 5፡46 ዕብ 10፡1-10፣ ሮሜ 10፡4 ገላ 4፡4-5 ቆላ 2፡17

# *የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)*

### *የጌታ ቀን፡ 7*

***<u>20. ታዲያ በአዳም ምክንያት ስለጠፉ የሰው ልጆች ሁሉ በክርስቶስ ይድናሉን?</u>***

*ሀ)* አይድኑም

በእዉነተኛ እምነት ወደ ክርስቶስ መጥተው የተተከሉት እና ቸርነቱን ሁሉ ያገኙት ብቻ ይድናሉ።

ማቴ 7፡14 ዮሐ 3፡16፣18፣36 ሮሜ 11፡16-21

***<u>21. እዉነተኛ እምነት ምንድነው?</u>***

እውነተኛ እምነት እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጠልንን ሁሉ እንደ እውነት የያዝኩበት እርግጠኛ እውቀት ብቻ አይደለም፤ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ በወንጌል የሚፈጥረው፣ እግዚአብሔር ለሌሎች ብቻ ሳይሆን ለእኔ ደግሞ የኃጢአት ይቅርታን፣ ዘላለማዊ ጽድቅን እና ድነትን የሰጠኝ፣ በሙሉ ልብ የምታመነው ነው። እነዚህ በክርስቶስ ብቃት ብቻ የተሰጡ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው።

ዮሐ 17፡3 ፣ *ዕብ* 11፡1-3 *ያዕ* 2፡19፣ ሮሜ 4፡18-21 ፣ 5፡1 ፣10፡10፣ *ዕብ* 4፡14-16፣ ማቴ 16፡15-17 ዮሐ 3፡5 ሐዋ 16፡14፣ ሮሜ 1፡16 ፣ 101 1ቆሮ 1፡21፣ ገላ 2፡20፣ ሮሜ 1፡17 *ዕብ* 10፡10፣ ሮሜ 3፡21-26 ገላ 2፡16 ኤፌ 2፡8-10

**22. እንግዲህ ክርስቲያኖች ግዴታ ሊያምኑ የሚገባቸው ትምህርቶች የትኞች ናቸው?**

በወንጌል ተስፋ የተሰጡንንና በማያጠራጥር መንገድ በእውነተኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሃይማኖት ድንጋጌ በሆኑት

ዮሃ 20: 31, ማት 28: 20, 2ኛ ጴጥ 1: 21, 2ኛ ጢሞ 3: 15.

**23. እነዚህ የሃይማኖት ድንጋጌዎች የትኞች ናቸው?**

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።

ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፤ ከድንግል ማርያም በተወለደ፤ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፤ በተሰቀለ፤ በሞተ፤ በተቀበረ፤ ወደ ሲኦል በወረደ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፤ ወደ ሰማይ በወጣ፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ

ቀኝ በተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት፤ በኃጢአት ስርየት፤ በሥጋ ትንሣኤ፤ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።

***የጌታ ቀን 8***

**24. እነዚህ የሃይማኖት አናቅስት እንዴት ይከፈላሉ?**

በሶስት ክፍል ይከፈላሉ። የመጀመሪያው ክፍል ስለ እግዚአብሔር አብና ስለፍጥረታችን፣ ሁለተኛው ክፍል ስለ እግዚአብሔር ወልድና ስለ ድህነታችን፣ ሶስተኛው ክፍል ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስና መቀደሳችን ነው።

1 ጴጥ. 1:2; *1 ዮሐ. 5:7.

**25. በመለኮት አንድ ከሆነ ስለምን ስለ ሶስቱ አካላት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንናገራለን?**

ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ በዚህ መንገድ ራሱን ስለገለጠ፣ እነዚህም ሶስቱ አካላት አንድ፣ እውነተኛ፣ ዘላለማዊ አምላክ ስለሆነ።

[1] ዘዳ. 6:4. [2] ኢሳ. 61:1; መዝ. 110:1; ማቴ. 3:16—17; 28:19; 1 ዮሐ. 5:7; *2 ቆሮ. 13:14.

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

## ክፍል አንድ፤ ስለ እግዚአብሔር አብ

### የጌታ ቀን 9

**26. ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ ስትል ምን ማለትህ ነው?**

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም አባት (ሰማይንና ምድርን በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ከምንም ነገር የሠራ፣ እንዲሁም በዘላለማዊ ምክርና መግቦት የሚደግፈውና የሚያስተዳድር፣ ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አምላኬና አባቴ ያለ ምንም ጥርጥር ሙሉ በሙሉ የምመካበት ለነፍሴና ለሥጋዬ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ ይሰጠኛል; ከዚህም በላይ በእኔ ህይወት ውስጥ የሚያመጣውን ክፉ ነገር ሁሉ በዚህ የሃዘን ሸለቆ ውስጥ፣ ለእኔ ጥቅም እንዲሆን ይለውጠዋል፤ ይህን ሁሉ የሚያደርገው እርሱ ሁሉን ቻይ አምላክና በፍቃዱ ታማኝ አባት በመሆኑ ነው።

[1] ዘፍ. 1:31; መዝ. 33:6; *ቆላ. 1:16; *ዕብ. 11:3. [2] መዝ. 104:2—5; ማቴ. 10:30; ዕብ. 1:3; መዝ. 115:3; *ሐዋ 17:24—25. [3] ዮሐ. 1:12; ሮሜ. 8:15; ገላ. 4:5—7; ኤፌ. 1:5; *ኤፌ. 3:14—16; *ማቴ. 6:8. [4] መዝ. 55:22; ማቴ. 6:25—26; ሉቃ. 12:22—24; መዝ. 90:1—2. [5] ሮሜ. 8:28; *ሐዋ 17:27—28. [6] ሮሜ. 10:12. [7] ማቴ. 7:9—11; *ዘኁ. 23:19.

### የጌታ ቀን 10

**27. የእግዚአብሔር መግቦት ስትል ምን ማለትህ ነው?**

ሁሉን ቻይ የሆነውና በሁሉም ቦታ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል; በእጁ ሰማይን፣ ምድርንና ፍጥረታትን ሁሉ ደግፎ ያስተዳድራል። እፅዋትና ሣር፣ ዝናብና ድርቅ፣ ፍሬያማና ፍሬ አልባ ዓመታት፣ ምግብና መጠጥ፣ ጤናና ሕመም፣ ሀብትና ድህነት፣ በርግጥ ሁሉም ነገር በአጋጣሚ ሳይሆን በአባታዊ እጁ የሚከናወኑ ናቸው።

[1] ሐዋ 17:25—26. [2] ዕብ. 1:3. [3] ኤር. 5:24; *ሐዋ 14:17. [4] ዮሐ. 9:3. [5] ምሳ. 22:2; *መዝ. 103:19; ሮሜ. 5:3—5ሀ.

**28. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደፈጠረና አሁንም ሁሉን ነገር ደግፎ እንደሚይዝ ማወቅ ለእኛ ምን ይጠቅመናል?**

በመከራ ውስጥ እንድንታገስ፣ በብልጽግና እንድናመሰግነው፣ ወደፊት በሚደርስብን ነገሮች ሁሉ ምንም ነገር ከፍቅሩ እንዳይለየን በማወቅ፤ ፍጥረታት ሁሉ በእጁ ስለሆኑ ያለ እርሱ ፈቃድ መንቀሳቀስ ስለማይችሉ በታማኝ አምላካችንና አባታችን ላይ ጽኑ እምነት እንጥላለን። [1] ሮሜ. 5:3; ያዕ. 1:3; እዮ. 1:21. [2] ዘዳ. 8:10; 1ተሰ. 5:18. [3] ሮሜ. 8:35, 38—39. [4] እዮ 1:12; ሐዋ 17:25—28; ምሳ. 21:1; *መዝ. 71:7; *2 ቆሮ. 1:10.

## ክፍል ሁለት ስለ እግዚአብሔር ወልድ

### የጌታ ቀን 11

**29. የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፣ ማለትም አዳኝ ተብሎ የሚጠራው ለምንድነው?**

ምክንያቱም እርሱ ከኃጢአታችን የሚያድንና ያለ እርሱ በሌላ መዳን ማግኘት ስለማንችል ነው።

[1] ማቴ. 1:21; ዕብ. 7:25. [2] ሐዋ 4:12; *ሉቃ. 2:10—11

**30. ደህንነታቸውን "ከቅዱሳን" ከራሳቸው ወይም ከሌላ ቦታ የሚፈልጉ ሰዎች ብቸኛ አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ?**

አያምኑም በቃላቸው እንደሚያምኑ ቢናገሩም ነገር ግን ብቸኛ አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን በሥራቸው ይክዳሉ።

ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱ እውነት ሊሆን ይገባል፤ ኢየሱስ ፍጹም አዳኝ አይደለም፤ ወይም ይህን አዳኝ በእውነተኛ እምነት በመቀበል ለመዳናቸው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ በእርሱ ማግኘት አለባቸው.

[1] 1ቆሮ. 1:13, 30—31; ገላ. 5:4. [2] ኢሳ. 9:7; ቆላ. 1:20; 2:10; ዮሐ. 1:16; *ማቴ. 23:28.

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

## የጌታ ቀን 12

### 31. እርሱ ክርስቶስ ቅቡእ የተባለው ለምንድነው?

በእግዚአብሔር አብ የተሾመና በመንፈስ ቅዱስም የተቀባው እርሱ ሊቀ ነቢያትና መምህራችን ሊሆንልን፣ ቤዛችን በመሆን የእግዚአብሔርን ምሥጢር፣ ምክርና ፈቃድ በሙላት ሊገልጥልን፣ ብቸኛ ልቀ ካህናችን በመሆን ስጋውን አንዴ መስዋእት አድርጎ በማቅረብ ሊዋጀንና ከአብ ጋር ስለ እኛ ሊማልድ ዘወትር በህይወት በመኖር በቃሉና በመንፈሱ የሚያስተዳድረን ዘላለማዊ ንጉሳችን ለመሆንና በተቀበልነው መዳን እንዲያጸናንና በተቀበልነው መዳን ሊጠብቀን እርሱ ክርስቶስ ቅቡእ ተባለ። [1] ዕብ. 1:9. [2] ዘዳ. 18:15; ሐዋ 3:22. [3] ዮሐ. 1:18; 15:15. [4] መዝ. 110:4; ዕብ. 7:21. [5] ሮሜ. 5:9—10. [6] መዝ. 2:6; ሉቃ. 1:33; ማቴ. 28:18; *ኢሳ. 61:1—2; *1 ጴጥ. 2:24; *ራዕይ. 19:16.

### 32. ለምን ክርስቲያን ተባልህ?

ምክንያቱም እኔ በእምነት የክርስቶስ አካል በመሆኔ፣ የቅባቱም ተካፋይ የሆንሁና ለስሙም እመሰክር ዘንድ ራሴንም ለእርሱ የምስጋና መሥዋዕት አድርጌ አቀርብ ዘንድ ነው። ደግሞ በነጻ እና በበጎ ህሊና በዚህ ሕይወት ከኃጢያትና ከሰይጣን ጋር እንድዋጋ፣ በኋላም ከእርሱ ጋር ለዘላለም በፍጥረት ሁሉ ላይ እንድነግስ ነው።

[1] ሐዋ 11:26; 1ዮሐ. 2:27; *1ዮሐ. 2:20. [2] ሐዋ 2:17. [3] ማር. 8:38. [4] ሮሜ. 12:1; ራዕይ. 5:8, 10; 1ጴጥ. 2:9; ራዕይ. 1:6. [5] 1ጢሞ. 1:18—19. [6] 2 ጢሞ. 2:12; *ኤፌ. 6:12; *ራዕይ. 3:21

## የጌታ ቀን 13

### 33. እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን እያለ ክርስቶስ ለምን አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ?

ምክንያቱም ክርስቶስ ብቻውን ዘላለማዊና በባህርይው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣ እኛ ግን ስለ ስሙ በጸጋው የማደጎ የእግዚአብሔር ልጆች ነን።

[1] ዮሐ. 1:14, 18. [2] ሮሜ. 8:15—17; ኤፌ. 1:5—6; *1ዮሐ. 3:1.

### 34. ለምን ኢየሱስን "ጌታችን" ትለዋለህ?

ምክንያቱም በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን በክቡር ደሙ ሥጋችንና ነፍሳችንን ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ኃይል ሁሉ ዋጅቶ የራሱ እንድንሆን ስላደረገን ነው።

[1] 1ጴጥ. 1:18—19; 2:9; 1ቆሮ. 6:20; 7:23; *ሐዋ 2:36; *ቲቶ. 2:14; *ቆላ. 1:14.

*የጌታ ቀን 14*

**35. "በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም ተወለደ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?**

እውነተኛና ዘላለማዊ አምላክ የሆነውና ሁሌም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የሆነው የሰውን ባህርይ የድንግል ማርያምን ሥጋና ደም በመንፈስ ቅዱስ አሠራር በመንሳት ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ ወንድሞቹን በመምሰል እውነተኛ የዳዊት ዘር ይሆን ዘንድ ነው።

[1] ዮሐ. 1:1; ሮሜ. 1:3—4. [2] ሮሜ. 9:5. [3] ገላ. 4:4; ዮሐ. 1:14. [4] ማቴ. 1:18—20; ሉቃ. 1:35. [5]መዝ. 132:11. [6] ፊል. 2:7. [7] ዕብ. 4:15; *1ዮሐ. 5:20.

**36. በክርስቶስ ቅዱስ መፀነስ እና ልደት ምን ጥቅም ታገኛለህ?**

እርሱ መካከለኛችን በመሆኑ ንጹህና ፍጹም በሆነው ቅድስናው በእግዚአብሔር ፊት የተፀነስኩበትና የተወለድኩባቸውን ኃጢአቶቼን ይከድንልኛል።

[1] ዕብ. 2:16—17. [2] መዝ. 32:1; *1ዮሐ. 1:9

*የጌታ ቀን 15*

**37. መከራን ተቀበለ በሚለው ቃል ምን ተረዳህ?**

እርሱ፡ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን ሁሉ፡ በተለይም በሕይወቱ ፍጻሜ፡ በሥጋና በነፍስ የእግዚአብሔር ቁጣ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ሊገለጥ የነበረውን ኃጢአት ተሸከመ። በሕማማቱ እንደ ብቸኛ ማስተስረያ መስዋዕትነት፣ ሰውነታችንን እና ነፍሳችንን ከዘላለም ፍርድ ሊቤዠን፣ ለእኛ የእግዚአብሔርን ሞገስ፣ ጽድቅ እና የዘላለም ሕይወትን እንዲያስገኝልን መከራን ተቀበለ

[1] 1ጴጥ. 2:24; ኢሳ. 53:12. [2] 1ዮሐ. 2:2; 4:10; ሮሜ. 3:25—26; *መዝ. 22:14—16; *ማቴ. 26:38; *ሮሜ. 5:6.

**38. ለምንድነው በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን ፈራጅ ሆኖ መከራን የተቀበለው?**

እርሱ ንፁህ ሆኖ፣ ነገር ግን በጊዜያዊ ዳኛ የተኮነነ ሆኖ፣ ከተጋለጥንበት ከእግዚአብሔር ከባድ ፍርድ ነፃ እንዲያወጣን ነው።

[1] ሐዋ 4:27—28; ሉቃ. 23:13—15; ዮሐ. 19:4. [2] መዝ. 69:4; 2 ቆሮ. 5:21; *ማቴ. 27:24

**39. ከተሰቀለው ሌላ ሞትን ከሞተ የበለጠ ነገር አለን?**

አዎ [አለ]; በእኔ ላይ የነበረውን እርግማን ወስዶ በእርሱ ላይ እንዳኖረ ይህን ተረድቻለሁና። የመስቀል  ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና።

[1] ገላ. 3:13—14. [2] ዘዳ. 21:22—23; *ፊል. 2:8.

*የጌታ ቀን 16*

**40. ክርስቶስ ራሱን እስከ ሞት ድረስ ማዋረድ ለምን አስፈለገ?**

ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍትህና እውነት ለኃጢአታችን እርካታ በእግዚአብሔር ልጅ ሞት ካልሆነ በስተቀር በሌላ ሊሆን አይችልም።

[1] ዘፍ. 2:17. [2] ዕብ. 2:9; ሮሜ. 6:23

**41. ለምን ደግሞ "ተቀበረ"?**

በዚህም እርሱ በእውነት መሞቱን ለማረጋገጥ ነው።

[1] ማቴ. 27:59—60; ዮሐ. 19:38—42; ሐዋ. 13:29.

**42. እንግዲህ ክርስቶስ ስለ እኛ ከሞተ እኛ ደግሞ ለምን መሞት አስፈለገን?**

ሞታችን ኃጢአታችንን ለማርካት ሳይሆን፣ ነገር ግን ኃጢአትን የማስወገድና ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ልንገባ ብቻ ነው።

[1] ዮሐ. 5:24; ፊል. 1:23; ሮሜ. 7:24—25.

**43. ከላይ ከተቀመጡ በረከቶች በተጨማሪ ከክርስቶስ መስዋዕትነትና የመስቀል ሞት ሌላ ምን በረከቶችን እናገኛለን?**

ወደ ፊት ክፉ የሥጋ አሳብ በእኛ እንዳይነግሥ በእርሱ ሃይል አሮጌው ሰዋችን ተሰቀለ፣ ተቸንክሮ ተቀበረ። እንዲሁም ራሳችንን ለእርሱ የምስጋና መሥዋዕት አድርገን እናቀርብ ዘንድ ነው።

[1] ሮሜ. 6:6—8; ቆላ. 2:12. [2] ሮሜ. 6:12. [3] ሮሜ. 12:1; *2 ቆሮ. 5:15.

**44. "ወደ ሲኦል ወረደ" የሚለው ለምን ተጨመረ?**

በከባድ ፈተናዬ ውስጥ ጌታዬ ክርስቶስ በነፍሱ በመስቀል ላይና ከዚያ በፊት በተሰቃየው ጭንቀቱ፣ ህመሙና ድንጋጤው ሊገለጥ በማይችል ጭንቀት፣ ከሲኦል ስቃይና መከራ እንዳዳነኝ እርግጠኛ እንድሆን ነው።

[1] ኢሳ. 53:10; ማቴ. 27:46; *መዝ. 18:5; 116:3.

***የጌታ ቀን 17***

**45. ከክርስቶስ ትንሣኤ ምን ተጨማሪ ጥቅሞች አገኘን?**

በመጀመሪያ በትንሣኤው ሞትን ድል ነሥቶአል፤ በሞቱ ከዋጀን ጽድቅ ተካፋዮች ያደርገን ዘንድ ነው፤ ሁለተኛ፣ እኛ ደግሞ በእርሱ ኃይል ለአዲስ ሕይወት የተነሣን እንሆን ዘንድ ነው። በመጨረሻ፣ የክርስቶስ ትንሣኤ ለእኛ የተባረከ የትንሣኤያችን ዋስትና ነው።

[1] 1ቆሮ. 15:15,17, 54—55. ሮሜ. 4:25; 1ጴጥ. 1:3—4, 21. [2] ሮሜ. 6:4; ቆላ. 3:1—4; ኤፌ. 2:5. [3] 1ቆሮ. 15:12; ሮሜ. 8:11; *1ቆሮ. 15:20—21.

**46. "ወደ ሰማይ ዐረገ" የሚለውን ቃል እንዴት ተረዳህ?**

ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ፊት ከምድር ወደ ሰማይ እንደ ተወሰደ፣ እርሱም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ። ስለኛ በሰማይ በመኖር እንደሚቀጥል ነው የተረዳሁት

[1] ሐዋ 1:9; ማቴ. 26:64; ማር. 16:19; ሉቃ. 24:51. [2] ዕብ. 4:14; 7:24—25; 9:11; ሮሜ. 8:34. ኤፌ. 4:10. [3] ሐዋ 1:11; ማቴ. 24:30; *ሐዋ. 3:20—21.

**47. ክርስቶስ እንደ ተናገረው እንግዲህ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር አይደለምን?**

ክርስቶስ ሰው እና አምላክ ነው; ስለ ሰብአዊ ባህርይ በምድር ላይ የለም; ነገር ግን በአምላክነቱ፣ በግርማው፣ በጸጋውና በመንፈሱ፣ ከእኛ ዘንድ ከቶ ርቆ አያውቅም።

**48. ነገር ግን አምላክነቱ ባለበት ሰብዓዊ ባህርይው ከሌለ እነዚህ በክርስቶስ ያሉት ሁለቱ ባህርያት እርስ በርሳቸው አልተለያዩምን?**

በፍፁም አይደለም፣ ምክንያቱም መለኮት የማይመረመርና በሁሉም ቦታ የሚገኝ ስለሆነ፣ እሱ ራሱ በነሳው የሰው ልጅ ባህርይ ብቻ የማይወሰንና በአንድ አካል ሆኖ ይኖራል።

[1] ማቴ. 28:20. [2] ማቴ. 26:11; ዮሐ. 16:28; 17:11. [3] ዮሐ. 14:17—18; 16:13; ኤፌ. 4:8; ማቴ. 18:20; *ዕብ. 8:4

***የጌታ ቀን 18***

**49. የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረጉ ለእኛ ምን ይጠቅመናል?**

በመጀመሪያ እርሱ በሰማያት ባለው አባቱ ፊት ጠበቃችን ነው; ሁለተኛ፣ ሥጋችን በሰማያት እንዳለ የተረጋገጠ ዋስትና ሆኖን እርሱ ራስ ሆኖ እኛን ደግሞ አካሎቹን ለራሱ ይወስዳል። በሶስተኛ ደረጃ መንፈሱን እንደ እርስት መያዣ ልኮልናል፣ በእርሱ ኃይል በላይ ያለውን የምንፈልገው ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።

[1] 1ዮሐ. 2:1; ሮሜ. 8:34. [2] ዮሐ. 14:2; 20:17; ኤፌ. 2:6. [3] ዮሐ. 14:16; ሐዋ. 2:33; 2 ቆሮ. 5:5. [4] ቆላ. 3:1; *ዮሐ. 14:3; *ዕብ. 9:24.

**50. "በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ" የሚለው ለምን ተጨመረ?**

አብ ሁሉን የሚገዛበት፣ ለቤተክርስቲያኑ ራስ ሆኖ ይታይ ዘንድ፣ ክርስቶስ ለዚህ ዓላማ ወደ ሰማይ አረገ።

[1] ኤፌ. 1:20—23; ቆላ. 1:18. [2] ዮሐ. 5:22; *1ጴጥ. 3:22; *መዝ. 110:1.

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም ( እ.ኤ.አ 1563)

## የጌታ ቀን 19

### 51. ይህ ራሳችን የሆነው የክርስቶስ ክብር ለእኛ ምን ይጠቅመናል?

በመጀመሪያ፣ በመንፈስ ቅዱስ በአካሉ ላይ ሰማያዊ ጸጋን ያፈሰሰልን፤ ከዚያም በኃይሉ የሚጠብቀንና ከጠላቶች ሁሉ የሚታደገን ነው።

[1] ኤፌ. 4:10—12. [2] መዝ. 2:9; ዮሐ. 10:28—30; *1ቆሮ. 15:25—26; *ሐዋ 2:33.

### 52. “ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ዳግመኛ ይመጣል” የሚለው ምን አይነት መጽናኛህ ነው?

በመከራዬና በስደቴ ሁሉ አሳቤን ከፍ አድርጌ እጠባበቃለሁ፤ አስቀድሞ ስለ እኔ ለእግዚአብሔር ፍርድ ራሱን አቀረበ እርግማኑንም ሁሉ ከእኔ አርቆ ከሰማይ ፈራጅ ሆኖ ይመጣ ዘንድ እጠባበቃለሁ። እርሱ ጠላቶቼን ሁሉ ወደ ዘላለማዊ ፍርድ ይጥላል፣ ነገር ግን ከተመረጡት ሁሉ ጋር ወደ እርሱ፣ ወደ ሰማያዊ ደስታ እና ክብር ያስገባኛል።

[1] ሉቃ. 21:28; ሮሜ. 8:23—24; ፊል. 3:20—21; ቲቶ. 2:13. [2] 2 ተሰ. 1:6, 10; 1ተሰ. 4:16—18; ማቴ. 25:41. [3] *ሐዋ 1:10—11; *ዕብ. 9:28.

## ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

## የጌታ ቀን 20

### 53. ስለ "መንፈስ ቅዱስ" ምን ታምናለህ?

አንደኛ፣ እርሱ ከአብና ከወልድ ጋር የዘላለም አምላክ መሆኑን። ሁለተኛ፣ ለእኔ ደግሞ የተሰጠኝ በእውነተኛ እምነት የክርስቶስ የመዳን በረከቶች ተካፋይ ሊያደርገኝ፣ ሊያጽናናኝና ለዘላለም ከኔ ጋር ሊኖር እንደሆነ።

[1] ዘፍ 1:2; ኢሳ. 48:16; 1ቆሮ. 3:16; 6:19; ሐዋ. 5:3—4. [2] ማቴ. 28:19; 2 ቆሮ. 1:21—22. [3] 1ጴጥ. 1:2; 1ቆሮ. 6:17. [4] ሐዋ 9:31. [5] ዮሐ. 14:16; 1ጴጥ. 4:14; *1ዮሐ. 4:13; *ሮሜ. 15:13.

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

## *የጌታ ቀን 21*

**54. ስለ "ቅድስት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን" ምን ታምናለህ?**

ከመላው የሰው ዘር ከአለም መጀመሪያ እስከ አለም ፍጻሜ የእግዚአብሔር ልጅ በመንፈሱና በቃሉ በእውነተኛ እምነት የምትስማማ የተመረጠች ህብረትን ይሰበስባል፣ ይከላከላል፣ ለራሱ ለዘላለም ህይወት ይጠብቃል፤ እኔም ለዘ ላለም የዚህ ኅብረት አባል ሆኜ እኖራለሁ። [1] ዘፍ. 26:4. [2] ዮሐ. 10:10. [3] ኤፌ.. 1:10—13. [4] ሮሜ. 1:16; ኢሳ. 59:21; ሮሜ. 10:14—17; ኤፌ. 5:26. [5] ሮሜ. 8:29—30; ማቴ. 16:18; ኤፌ. 4:3—6. [6] ሐዋ 2:46; መዝ. 71:18; 1ቆሮ. 11:26; ዮሐ. 10:28—30; 1ቆሮ. 1:8—9. [7] 1ዮሐ. 3:21; 1ቆሮ. 2:19; *ገላ. 3:28.

**55. ስለ ቅዱሳን ኅብረት" ምን ተረዳህ?**

በመጀመሪያ፣ አማኞች፣ ሁሉ በአንድነት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል በመሆናቸው በጸጋዎችና በስጦታዎቹ ሁሉ ከእርሱ ጋር ተካፋዮች መሆናቸውን፣ ሁለተኛው እያንዳንዱ ሰው ስጦታውን በደስታ ለሌሎች ጥቅምና ደህንነት ሊጠቀምበት ግዴታው መሆኑን ማወቅ አለበት።

[1] 1ዮሐ. 1:3. [2] 1ቆሮ. 12:12—13, 21; 13:5—6; ፊል. 2:4—6; *ዕብ. 3:14.

56. **ስለ ኃጢአት ስርየት" ምን ታምናለህ?**

እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ መስዋእት አንዴ ኃጢአቴንና በሕይወቴ ዘመን ሁሉ መታገል ያለብኝን የሃጢአት ተፈጥሮዬን ከእንግዲህ ወዲህ እንደማያስብና ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ከቶ እንዳይፈረድብኝ የክርስቶስ ጽድቅን እንዲያው ይቆጥርልኛል።

[1] 1ዮሐ. 2:2. [2] 2 ቆሮ. 5:19, 21; ሮሜ. 7:24—25; መዝ. 103:3, 10—12; ኤር. 31:34; ሮሜ. 8:1—4. [3] ዮሐ. 3:18; *ኤፌ. 1:7; *ሮሜ. 4:7—8; 7:18.

## *የጌታ ቀን 22*

**57. ከአካል ትንሣኤ" ምን ማጽናኛ ታገኛለህ?**

ከዚህ ህይወት በኋላ ነፍሴ ብቻ ሳይሆን ስጋዬም ራስ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ይወሰዳል፣ ነገር ግን ይህ በክርስቶስ ሃይል የተነሳው ሥጋዬ ከነፍሴ ጋር አንድ በመሆን የክርስቶስን የከበረ አካል እንዲመስል ይለወጣል።

[1] ሉቃ. 23:43; ፊል. 1:21—23. [2] 1ቆሮ. 15:53—54; ኢዮ 19:25—27; 1ዮሐ. 3:2

**58. በዘላለም ህይወት አምናለሁ በሚለው የሃይማኖት ድንጋጌ ምን ማጽናኛ አግኝተሃል?**

የዘላለም ደስታ መጀመሪያ አሁን በልቤ ስለተሰማኝ ከዚህ ህይወት በኋላ ደግሞ ምሉእ የሆነውን "ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበውን" ፍጹም መዳንን እወርሳለሁ። በዚህም እግዚአብሔርን ለዘላለም እያመሰገንሁ ኖራለሁ።

[1] 2 ቆሮ. 5:2—3. [2] 1ቆሮ. 2:9. [3] ዮሐ. 17:3; *ሮሜ. 8:23; *1ጴጥ. 1:8.

### *የጌታ ቀን 23*

**59. ይህን ሁሉ ማመን ግን ምን ይጠቅመሃል?**

እኔ በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ጻድቅ ሆኜ የዘላለም ህይወት ወራሽ እንድሆን ነው።

[1] ዕን. 2:4; ሮሜ. 1:17; ዮሐ. 3:36; *ቲቶ. 3:7; *ሮሜ. 5:1; *ሮሜ. 8:16.

**60. አንተ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ሆንህ?**

ኅሊናዬ ቢወቅሰኝም፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ በጽኑ ብተላለፍም፣ ሁልጊዜ ወደ ክፋት ሁሉ ባዘነብልም፣ ነገር ግን፣ እግዚአብሔር፣ ያለ ምንም ስራዬ በጸጋው ብቻ የክርስቶስን መስዋእት፣ ጽድቅና ቅድስና ለኔ በመቁጠር ደግሞም ከቶ ኃጢአት እንዳልሠራሁ ተደርጌ ክርስቶስ ለእኔ ያደረገልኝን መታዘዝ ሁሉ ፈጽሜ እንደፈጸምሁ በልቤ በማመን በኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ እምነት ብቻ ጻድቅ ሆንኩኝ።

[1] ሮሜ. 3:21—25; ገላ. 2:16; ኤፌ. 2:8—9; ፊል. 3:9. [2] ሮሜ. 3:9—10. [3] ሮሜ. 7:23. [4] ቲቶ. 3:5. [5] ሮሜ. 3:24; ኤፌ. 2:8. [6] 1ዮሐ. 2:2. [7] 1ዮሐ. 2:1; ሮሜ. 4:4—5; 2 ቆሮ. 5:19. [8] 2 ቆሮ. 5:21. [9] ዮሐ. 3:18; *ሮሜ. 3:28; *ሮሜ. 10:10.

**61. አንተ በእምነት ብቻ ጻድቅ ነኝ ለምን ትላለህ?**

ስለ እምነቴ ብቁ መሆኔ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አገኛለሁ ብዬ ሳይሆን ነገር ግን የክርስቶስ መስዋእት፣ ጽድቅና ቅድስና ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቄ ስለሆነና በእምነት ብቻ ካልሆነ በቀር ያንኑ መቀበልና ለራሴ ተግባራዊ ስለማልችል ነው።

[1] 1ቆሮ. 1:30; 2:2. [2] 1ዮሐ. 5:10. *ኢሳ. 53:5; *ገላ. 3:22; *ሮሜ. 4:16.

### የጌታ ቀን 24

**62. ነገር ግን ለምንድነው መልካም ስራችን በሙሉ ወይም በእግዚአብሔር ፊት የጽድቃችን ክፍል ሊሆን ያልቻለው?**

ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፍርድ ወንበር ፊት የሚቆመው ፅድቅ ፍጹምና ሙሉ በሙሉ ከመለኮታዊ ህግ ጋር የሚስማማ መሆን አለበት፣ ነገር ግን በዚህ ህይወት ውስጥ ያለን መልካም ስራዎቻችን እንኳን ሁሉም ፍጽምና የጎደላቸውና በኃጢአት የረከሱ ናቸው።

[1] ገላ. 3:10; ዘዳ. 27:26. [2] ኢሳ. 64:6; *ያዕ. 2:10; *ፊል. 3:12

**63. እግዚአብሔር በዚህና ወደፊት በሚመጣው ሕይወት ለመልካም ሥራችን የሚሸልመን ዋጋ የለምን?**

ይህ ሽልማት የጸጋ እንጂ የመልካም ስራችን ዋጋ አይደለም።

[1] ሉቃ. 17:10; *ሮሜ. 11:6

**64. ነገር ግን ይህ ትምህርት ሰዎችን ግድየለሾችና ሰነፎች አያደርጋቸውምን?**

በምንም መልኩ፡ በእውነተኛ እምነት ወደ ክርስቶስ የተተከሉ አማኞች የምስጋና ፍሬዎችን አለማፍራት አይችሉም

[1] ማቴ. 7:18; *ሮሜ. 6:1—2; *ዮሐ. 15:5.

### ቅዱስ ምስጥራት

### የጌታ ቀን ፡ 25

<u>**65. ከክርስቶስ እና ከባርኮቶቹ ጋር የምንካፈለው በእምነት ብቻ ነው፡ ታዲያ ይህ እምነት ከየት ይመጣል?**</u>

መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ በወንጌል ስብከት ያመነጨዋል፣ በቅዱስ ምስጥራትም ያጸናዋል።

ዮሐንስ 3:5; 1 ቆሮ. 2:10-14; ኤፌ. 2፡8፣ ሮሜ. 10:17; 1 ጴጥ. 1፡23-25፣ ማቴ. 28:19-20; 1 ቆሮ. 10፡16

***66. ቅዱስ ምስጥራት ምንድን ናቸው?***

ቅዱስ ምስጥራት ይታያሉ፣ ቅዱሳት ምልክቶች እና ማኅተሞች ናቸው። እኛ ስንጠቀምባቸው የወንጌልን ተስፋ የበለጠ እንድናስተውል የሚያደርጉን እና የተስፋውን ቃል በግልጽ እንዲያስተምረን በእግዚአብሔር የተመሰረቱ ናቸው። በክርስቶስ አንድ መስዋዕትነት የኃጢአትን ስርየትና የዘላለምን ሕይወት በጸጋ ይሰጠን ዘንድ የእግዚአብሔር የወንጌል ቃል ኪዳን ይህ ነው። በመስቀል ላይ ተፈጽሟል።

ዘፍ 17:11; ዘዳ. 30:6; ሮም. 4፡11፣ ማቴ. 26:27-28; የሐዋርያት ሥራ 2:38; ዕብ. 10፡10

***67. ሁለቱም ማለትም ቃሉ እና ምስጥራት በእምነታችን ላይ እንዲያተኩሩ የታሰቡ ከሆነ በመስቀል ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ላይ እንደ ብቸኛ የመዳናችን መሠረት ናቸውን?***

አዎ! በወንጌል አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል እናም በቅዱስ ቁርባን ድነታችን ሁሉ በመስቀል ላይ በክርስቶስ አንድ መስዋዕትነት ላይ ያረፈ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሮም. 6:3; 1 ቆሮ. 11:26; ገላ. 3፡27

***68. ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስንት ምሥጢራትን አቋቋመ?***

ሁለት፡- ቅዱስ ጥምቀት እና ቅዱስ ቁርባን

ማቴ. 28:19-20; 1 ቆሮ. 11፡23-26

## *ቅዱስ ጥምቀት*

### *የጌታ ቀን፡ 26*

***69. ቅዱስ ጥምቀት የክርስቶስ አንድ የመስቀል ላይ መስዋዕትነት አንተን በግል እንደሚጠቅምህ የሚያስታዉስህ እና የሚያረጋግጥልህ እንዴት ነው?***

በዚህ መንገድ፡- ክርስቶስ ይህንን ውጫዊ መታጠብን አቋቋመ እናም ውሃ ከሰውነት ቆሻሻን እንደሚያጸዳው ደሙ እና መንፈሱ የነፍሴን ርኩሰት ማለትም ኃጢአቶቼን ሁሉ በእርግጥም እንደሚያጥቡ ቃል ገባ።

የሐዋርያት ሥራ 2፡38፣ ማቴ. 3:11; ሮም. 6:3-10; 1 ጴጥ. 3፡21

***70ኛ ጥያቄ፡- በክርስቶስ ደም እና መንፈስ መታጠብ ማለት ምን ማለት ነው?***

በክርስቶስ ደም መታጠብ ማለት እግዚአብሔር በጸጋው፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የተነሳ ኃጢአታችንን በመስቀሉ መስዋዕትነት ይቅር ብሎናል ማለት ነው።

በክርስቶስ መንፈስ ታጥበናል ማለት የክርስቶስ አባላት እንድንሆን መንፈስ ቅዱስ አድሶናል እንዲሁም ቀድሶናል ማለት ነው፣ ስለዚህም አብዝተን ለኃጢአት እየሞትን ቅዱሳን እና ያለ ነውር እንድንሆን ነው።

ዘካ. 13:1; ኤፌ. 1:7-8; ዕብ. 12:24; 1 ጴጥ. 1:2; ራዕ 1፡5

ሕዝቅኤል. 36:25-27; ዮሐንስ 3:5-8; ሮሜ. 6:4; 1 ቆሮ. 6:11; ቆላ. 2፡11-12

*71. በጥምቀት ውሃ እንደታጠብን እንዲሁ ደግሞ በደሙና በመንፈሱ እንድንታጠብ ክርስቶስ ተስፋ የገባልን የት ነው?*

ጥምቀትን በመሰረተ ጊዜ እንዲህ ሲል ተናገረ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።"

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።"

ይህ የተስፋ ቃል ቅዱሳት መጻሕፍት ጥምቀትን "የዳግም መወለድ ውኃ" እና የኃጢአት መታጠብ ብለው በድጋሜ ይጠሩታል።

ማቴ. 28፡19፣ ማር. 16፡16፣ ቲቶ. 3፡5፣ የሐዋርያት ሥራ 22፡16

***የጌታ ቀን፡ 27***

*72. ይህ ውጫዊ በውኃ መታጠብ ራሱ ኃጢአትን ያጥባልን?*

አይደለም፣ ከኃጢያት ሁሉ የሚያነጻን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እና መንፈስ ቅዱስ ብቻ ናቸው።

ማቴ. 3:11; 1 ጴጥ. 3:21; 1ኛ ዮሐንስ 1፡7

*73. ለምንድነው መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን የዳግም ልደት ውሃ እና የኃጢያት መታጠብያ ያለው?*

እግዚአብሔር ለእነዚህ ቃላት በቂ ምክንያት አለው። ሲጀመር እግዚአብሔር ይህንን ሊያስተምረን ይፈልጋል፣ ይኸውም፡- ውሃ ከሰውነት ውስጥ ቆሻሻን እንደሚያስወግድ የክርስቶስ

ደም እና መንፈስ ኃጢአታችንን ያስወግዳል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን፣ እግዚአብሔር በዚህ መለኮታዊ ዋስትና እና ምልክት፣ ሰውነታችን በውሃ እንደሚታጠበው ሁሉ ከኃጢአታችን በመንፈስ እንደታጠብን ሊያረጋግጥልን ይፈልጋል፡፡

1 ቆሮ. 6:11; ራእይ 1:5; 7፡14፣ የሐዋርያት ሥራ 2:38; ሮም. 6:3-4; ገላ. 3፡27

## *74. ሕፃናትም መጠመቅ አለባቸው?*

አዎ! ሕፃናት እና ጎልማሶች በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እና ሰዎች ውስጥ ተካተዋል፣ እና እነሱ፣ ከአዋቂዎች ያላነሱ፣ በክርስቶስ ደም እና እምነት በሚፈጥረው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከኃጢአት ነጻ እንደሚወጡ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ ስለዚህ የቃል ኪዳኑ ምልክት በሆነው በጥምቀት እነሱም በክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ውስጥ መካተት እና ከማያምኑ ልጆች ተለይተው ሊታወቁ ይገባል፡፡ ይህም በብሉይ ኪዳን በግርዛት የተፈጸመ ሲሆን አሁን ደግሞ በአዲስ ኪዳን በጥምቀት ተተካ፡፡

ዘፍ 17:7; ማቴ. 19፡14፣ ኢሳ. 44:1-3; የሐዋርያት ሥራ 2:38-39; 16፡31፣ የሐዋርያት ሥራ 10:47; 1 ቆሮ. 7፡14 ዘፍ.17፡9-14፣ ቆላ.2፡11-13

## *የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ቁርባን*

### *የጌታ ቀን፡ 28*

## *75. ቅዱስ ቁርባን በክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው አንድ መስዋዕትነት እና በጥቅሞቹ ሁሉ እንደምትካፈሉ እንዴት ያስታውስሃል እና ያረጋግጥልሃል?*

በዚህ መንገድ፡-ክርስቶስ እኔን እና አማኞችን ሁሉ ለእርሱ መታሰቢያ ይህን ቍርስራሽ እንጀራ ለመብላት ይህንንም ጽዋ ለመጠጣት እንደሚገባን አዞናል፡፡

በዚህ ትእዛዝ እነዚህ ተስፋዎች ይመጣሉ፡- በመጀመሪያ፣ የጌታ እንጀራ ለእኔ ሲቆረስ እና ጽዋው ሲሰጠኝ በእርግጠኝነት በአይኖቼ እንደማየው ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ በመስቀሉ ላይ ስጋው ተላልፎ ተሰጥቶ ለእኔ ተቆራርሶልኛል እንዲሁም ደሙ ፈሶልኛል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ከአስተናጋጁ እጅ በምቀበለው እርግጠኝነት ልክ፣ በአፌ የጌታን እራት እና ጽዋ እንደምቀምሰው ሁሉ፣ የክርስቶስ ስጋ እና ደም እርግጠኛ ምልክት ይሆን ዘንድ ተሰጠኝ፣

በዚህ እርግጠኝነት ልክ ነብሴን ለዘለአለም ህይወት በተሰቀለው ስጋው እና በፈሰሰው ደሙ ያድሳታል ፣ ያረሰርሳታል።

ማቴ. 26:26-28; ማርቆስ 14:22-24; ሉቃስ 22:19-20; 1 ቆሮ. 11፡23-25

## *76. የተሰቀለውን የክርስቶስን ሥጋ መብላትና የፈሰሰውን ደሙን መጠጣት ማለት ምን ማለት ነው?*

የክርስቶስን ስቃይ እና ሞት ሁሉ እና በዚህም የሆነውን የኃጢአትን ስርየት እና የዘላለም ህይወትን ለማግኘት በሚያምን ልብ መቀበል ማለት ነው። ነገር ግን ከዚህም የበለጠ ትርጉም አለው። በክርስቶስም እና በእኛ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ በኩል፣ ወደ ክርስቶስ የተባረከ አካል የበለጠ አንድ እየሆንን እንኄዳለን ።

ስለዚህም ምንም እንኳን እርሱ በሰማይ እኛም በምድር ብንሆን የሥጋው ሥጋ፣ ከአጥንቱም ከአጥንት ነን።የአካላችን ብልቶች በአንድ ነፍስ እንደ ሆኑ በአንድ መንፈስ ለዘላለም እንኖራለን ፣ እንመራለንም።

ዮሐ 6:35, 40, 50-54፣ ዮሐ 6:55-56; 1 ቆሮ. 12፡13 የሐዋርያት ሥራ 1:9-11; 1 ቆሮ. 11:26; ቆላ.3፡1፣ 1 ቆሮ. 6:15-17; ኤፌ. 5:29-30; 1ኛ ዮሐንስ 4፡13፣ ዮሐንስ 6:56-58; 15:1-6; ኤፌ. 4:15-16; 1ኛ ዮሐንስ 3፡24

## *77. ምእመናንን ይህን ቍርስራሽ እንጀራ ሲበሉና ይህን ጽዋ ሲጠጡ በእርግጠኝነት በአካሉና በደሙ ለማረስረስ እና ለማደስ ክርስቶስ ተስፋ የገባው የት ነው?*

የቅዱስ ቁርባንን ምስጢር ክርሰቶስ ሲያስጀምር፡- “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።“ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።”

ይህ የተስፋ ቃል በእዚህ ቃል በጳዉሎስ በድጋሜ እንዲህ ተነግሯል፡-“የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ

ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።"

1ኛ ቆሮ.11፡23-26፣ 1ኛ ቆሮ.10፡16-17

## *የጌታ ቀን፡ 29*

### *78. እንጀራውና ወይኑ ትክክለኛው የክርስቶስ ሥጋና ደም ይሆናሉን?*

አይደለም። የጥምቀት ውሃ ወደ ክርስቶስ ደም እንደማይለወጥ እና ኃጢአትን በራሱ እንደማያጥብ ነገር ግን በቀላሉ የእነዚህ ነገሮች መለኮታዊ ምልክት እና ማረጋገጫ እንደሆነ ሁሉ ቅዱስ ቁርባን ቅዱስ እንጀራም ፣ ምንም አንኳን የምስጢረ ቁርባንን ተፈጥሮ እና ቋንቋ በመጠበቅ የክርስቶስ አካል ተብሎ ቢጠራም፤እውነተኛ የክርስቶስ አካል ሊሆን አይችልም።

ኤፌ. 5:26; ቲት. 3፡5፣ ማቴ. 26፡26-29፣ 1ቆሮ. 10:16-17; 11፡26-28፣ ዘፍ 17:10-11; ዘፀ. 12:11, 13; 1ቆሮ.10፡1-4

### *79. ታዲያ ክርስቶስ ኅብስቱን ሥጋዉ እንደሆነ ጽዋውን ደግሞ ደሙ ወይም በደሙ ያለውን አዲስ ኪዳን ብሎ የጠራው፣ ደግሞም ጳውሎስ ቃላቱን የተጠቀመው የክርስቶስ ሥጋ እና ደም እንደመካፈል አድርጎ የተጠቀመው ለምንድነው?*

ክርስቶስ ለእነዚህ ቃላት በቂ ምክንያት አለው። እንጀራና ወይን ጊዜያዊ ሕይወትን እንደሚመግቡት ሁሉ የተሰቀለው ሥጋውና የፈሰሰው ደሙ የነፍሳችን እውነተኛ ምግብና መጠጥ ለዘለዓለም ሕይወት መሆኑን ሊያስተምረን ይፈልጋል።

ከሁሉም በላይ ግን፣ በዚህ በሚታይ ምልክትና ቃል ኪዳን፣ በአፋችን እነዚህን ቅዱሳን ምልክቶች በመታሰቢያው እንደተቀበልን ሁሉ፣ እኛም በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከእውነተኛ ሥጋውና ከደሙ ተካፋዮች እንድንሆን ሊያረጋግጥልን ይፈልጋል። እንዲሁም ደግሞ እኛ በግላችን መከራ እንደተቀበልን እና ለኃጢአታችን የሚያረካ መስዋዕት እንዳደረግን ያህል የእርሱ መከራና ታዛዥነት የእኛ መሆኑን ሊያስተምረን ይፈልጋል።

ዮሐ 6:51, 55፣ 1 ቆሮ. 10:16-17; 11፡26፣ ሮሜ. 6፡5-11

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

## የጌታ ቀን ፡ 30

### *80. ቅዱስ ቁርባን ከሮማ ካቶሊክ የቁርባን መለወጥ የሚለየው እንዴት ነው?*

ቅዱስ ቁርባን ኃጢአታችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ የተሰረየልን በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ መስዋዕት እንደሆነ ይነግረናል፣ ይህንንም እርሱ ራሱ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ፈጽሟል። ደግሞም መንፈስ ቅዱስ እኛን እንድንሰግድለት በሚፈልግበት በአባቱ ቀኝ በሰማያት ወዳለው ከእውነተኛው አካሉ ጋር ወደ ሚሆነው ወደ ክርስቶስ ውስጥ እንደገባን ያውጃል።

[ነገር ግን የቁርባን መለወጥ እንደሚያስተምረው ክርስቶስ በየዕለቱ በካህናቱ ካልቀረበላቸው በቀር ሕያዋንና ሙታን ኃጢአታቸው በክርስቶስ መከራ ይቅር አይባልም የሚለዉን ነው። በተጨማሪም ክርስቶስ በአካል በኅብስትና በወይን ሥር እንደሚገኝ ያስተምራል ስለዚህም ክርስቶስ ሊሰገድበት ይገባል የሚል ነገር ያስተምራል። ስለዚህም ቅዳሴ በመሠረቱ የኢየሱስ ክርስቶስን አንድ መስዋዕትነትና መከራ መካድ እና የሚኮነን ጣዖት አምልኮ እንጂ ሌላ አይደለም።

ዮሐ 19:30; ዕብ. 7:27; 9:12, 25-26; 10:10-18 1 ቆሮ. 6:17; 10፡16-17፣ የሐዋርያት ሥራ 7:55-56; ዕብ. 1:3; 8፡1፣ ማቴ. 6:20-21; ዮሐንስ 4:21-24; ፊል. 3:20; ቆላ.3፡1-3

### *81. ወደ ጌታ ማዕድ መምጣት ያለበት ማን ነው?*

በኃጢአታቸው ምክንያት በራሳቸው ያልተደሰቱ፣ ነገር ግን ኃጢአታቸው እንደተሰረየላቸው እና ቀሪው ድካማቸው በክርስቶስ መከራና ሞት እንደተሸፈነ የሚተማመኑ፣ እና ደግሞ እምነታቸውን ለማጠናከር እና የተሻለ ሕይወት ለመምራት የበለጠ እና የበለጠ የሚፈልጉ። ግብዞችና ንስሐ የማይገቡ ግን በራሳቸው ላይ ፍርድን ይበላሉ ፣ ይጠጣሉም።

1 ቆሮ. 10:19-22; 11፡26-32

### 82. እንግዲህ በኃጢአታቸው ንሰሃ ያልገቡና በሕይወታቸው ትክክለኛ የሕይወት ልምምድ የሌላቸው ወደ ጌታ እራት እንዲቀርቡ ይፈቀዳል?

አይፈቀድም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ረክሷልና ቁጣውም በመላው ማኅበረ ጉባኤ ላይ ይገለጣል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስና እንደ ሐዋርያቱ ትእዛዝ እነዚህን ሰዎች በተሰጣት የማሰርና የመፍታት ስልጣን ተጠቅማ ህይወታቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ እስከ ማግለል ድረስ ትደርሳለች።

[1] 1 ቆሮ. 11:20, 34a; ኢሳ. 1:11—15; 66:3; ኤር. 7:21—23; መዝ. 50:16—17; ማቴ. 7:6; 1ኛ ቆሮ. 11:30—32; ቲት. 3:10—11; 2 ተሰ. 3፡6፡፡

### *የጌታ ቀን 31*

**83. የመፍታትና የማሰር ቁልፎች ምንድን ናቸው?**

የቅዱስ ወንጌል ስብከት እና ክርስቲያናዊ ዲስፕሊን፡፡ በእነዚህ በሁለቱ መንግሥተ ሰማያት ለአማኞች የተከፈተና ለማያምኑ ደግሞ የተዘጋች ናት፡፡

[1] ማቴ. 16:18—19; 18:18; ዮሐ. 20:23; ሉቃ. 24:46—47; 1ኛ ቆሮ. 1፡23—24፡፡

**84. መንግሥተ ሰማያት በቅዱስ ወንጌል ስብከት የሚከፈተውና የሚዘጋው እንዴት ነው?**

በክርስቶስ ትእዛዝ መሰረት በእውነተኛ እምነት በወንጌል የተስፋ ቃል በተቀበሉ ቁጥር ኃጢአታቸው ሁሉ ከእግዚአብሔር ለሚያምኑ እንደሚሰረይላቸው አንዴና ለሁልጊዜ በግልጽ ይነገርና ምስክርነት ይሰጣል፡፡ ይህም በዚህ መንገድ የሚሆነው ለክርስቶስ ክብር ሲባል ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በማያምኑና ከስተታቸው በማይመለሱ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣና የዘላለም ፍርድ በእነርሱ ላይ ይኖራል፡፡

ዮሐ. 20:21—23; የሐዋርያት ሥራ 10:43; ኢሳ. 58:1; 2 ቆሮ. 2:15—16; ዮሐ. 8፡24፡፡

**85. መንግሥተ ሰማያት በክርስቲያናዊ ዲስፕሊን የተዘጋውና የሚከፈተው እንዴት ነው?**

በዚህ መንገድ ነው፡፡ እንደ ክርስቶስ ትእዛዝ በክርስትና ስም እየተመላለሱ ጤናማ ባልሆነ ትምህርት ወይም በሕይወታቸው ጤናማ ያልሆነ ምልልስ ውስጥ የሚመላለሱ ከሆነና ከብዙ ወንድማማችነት ምክር በኋላ ከስህተታቸው ወይም ከክፉ መንገዳቸው የማይመለሱ ከሆነ በነርሱ ላይ ቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተክርስቲያን ኃላፊዎች; የሚያቀርቡባቸውን ቅሬታዎች መስማት ቸል ቢሉ ቅዱሳን ምስጥራትን መከልከልና ከክርስቲያናዊ ህብረት መወገዝ፤ በእግዚአብሔር ራሱ ከክርስቶስ መንግስት የሚቆረጡበት ስርአት ሲሆን ከትምህርታቸው ከተመለሱና እውነተኛ ንሰሃ ካደረጉ፣ እንደገና እንደ ክርስቶስ አካልና እንደ ቤተክርስቲያኑ አባላት ድጋሚ ይቆጠራሉ፡፡

ማቴ. 18:15—18; 1 ቆሮ. 5:3—5, 11; 2 ተሰ. 3፡14—15; 2 ዮሐ. 1፡10—11

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( እ.ኤ.አ 1563)

## ክፍል ሦስት ፡ አመስጋኝነት

### የጌታ ቀን 32

**86. እንግዲህ በክርቶስ በኩል በጸጋው ያለ እኛ አንዳች መልካምነት ከመከራችን ከተዋጀን ለምን መልካም ስራን መስራት ግድ ሆነብን?**

ምክንያቱም፣ ክርስቶስ በደሙ ስለዋጀን እንዲሁም ደግሞ የእርሱን መልክ እንድመስል በመንፈስ ቅዱስ ስላደሰን ይህም ደግሞ ለእግዚአብሔር በረከት ምላሽ በመላው ሕይወታችን እራሳችንን በእርሱ ፊት አመስጋኞች እንሆን ዘንድ ነው። በዚህም እርሱ በእኛ እንዲከበር እኛም እንደዚህ ባለው ፍሬ እምነታች እንድናጸና እና በእኛ እግዚአብሔርን መምሰል አካሄድ ሌሎችን ለክርስቶስ እንማርክ ዘንዳ ነው።

[1] ሮሜ. 6: 13፤ 12:1—2; 1 ጴጥ. 2: 5, 9—10፤ 1ቆሮ. 6: 20። [2] ማቴ. 5: 16፤ 1 ጴጥ. 2: 12. [3] ማቴ. 7: 17—18፤ ገላ. 5: 6, 22—23 [4] ሮሜ. 14: 19፤ 1 ጴጥ. 3: 1—2፤ *2 ጴጥ. 1: 10.

**87. ታዲያ ካለማመስገን እና ንስሃ ካለመግባት ወደ እግዚአብሔር ዞር ያላሉት ሊድኑ አይችሉም?**

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ንጹሕ ያልሆነ ሰው ፣ ጣዖት አምላኪ ፣ አመንዝራ ፣ ሌባ ፣ መጎምጀት ፣ ሰካራም ፣ ስም አጥፊ ፣ ዘራፊ ወይም የመሳሰሉት የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ።

[1] 1 ቆሮ. 6: 9—10፤ ኤፌ. 5: 5—6፤ 1 ዮሐ. 3: 14—15

### የጌታ ቀን 33

**88. እውነተኛ ንስሃ እና መለወጥ ስንት ነገሮችን የያዘ ነው?**

ሁለት ነገሮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም የአሮጌው ሰው መሞትና የአዲሱ ሰውነት ህያውነት ነው።

[1] ሮሜ. 6: 4—6፤ ኤፌ. 4: 22—24፤ ቆላ. 3፥5—10፤ 1ቆሮ. 5: 7

**89. የአሮጌው ሰው መሞት ምንድነው?**

ከልብ ስለኃጢያት የሆነ ሃዘን ሃጢያትን እንድንጠላ እና ከኃጢያት በብዙ እንድመለስ ሲያደርገን ነው::

[1] ሮሜ. 8: 13፤ ኢዩኤል 2: 13

**90. አዲሱን ሰው ህያው ማድረግ ምንድነው?**

ከልብ የሆነ በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደስ መሰኘት ሲሆን እንደ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመልካም ስራ በመኖር ደስተኛ እንድንሆን ሲያደርገን ነው::

[1] ሮሜ. 5: 1፤ 14:17; ኢሳ. 57: 15 [2] ሮሜ. 8: 10—11፤ ገላ. 2: 20፤ *ሮሜ. 7: 22

**91. መልካም ስራ ምንድነው?**

ከእውነተኛ እምነት ብቻ ሚመነጭ እና እነደ እኛ መልካም አስተያየት ወይም እንደ ሰወች ት ዕዛዝ ሳይሆን በእግዚአብሔር ህግ ላይ የተመሰረተ ለእግዚአብሔር ክብር የተደረገ ነገር ነው::

[1] ሮሜ. 14: 23 [2] 1 ሳሙ. 15: 22፤ ኤፌ. 2: 10 [3] 1ቆሮ. 10: 31 [4] ዘዳ. 12: 32፤ ሕዝ. 20: 18, 20፤ ኢሳ. 29: 13 [5] ማቴ. 15: 9፤ *ዘኍ. 15: 39

## *የእግዚአብሔር ህግ*

**92. የእግዚአብሔር ህግ ምንድን ነው?**

እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦

***የመጀመሪያይቱ ትዕዛዝ***

ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ:: ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ::

***ሁለተኛይቱ ትዕዛዝ***

በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ:: አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.ኦ 1563)

ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።

**ሶስተኛይቱ ትዕዛዝ**

የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

**አራተኛይቱ ትዕዛዝ**

የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ፤ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም።

**አምስተኛይቱ ትዕዛዝ**

አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።

**ስድስተኛይቱ ትዕዛዝ**

አትግደል።

**ሰባተኛይቱ ትዕዛዝ**

አታመንዝር።

**ስምተኛይቱ ትዕዛዝ**

አትስረቅ።

**ዘጠነኛይቱ ትዕዛዝ**

በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።

*የሃይድልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)*

**አስረኛይቱ ትዕዛዝ**

የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።

[1] ዘፀ. 20፤ ዘዳ. 5፤ *ማቴ. 5፡ 17—19፤ *ሮሜ. 10፡ 5፤ *ሮሜ. 3፡ 31; *መዝ. 119፡ 9

***የጌታ ቀን 34***

**93. እነዚህ ትእዛዛት የተከፋፈሉት እንዴት ነው?**

በሁለት ገበታ ሲሆን የመጀመሪው በአራቱ ትዕዛዛት በኩል ለእግዚአብሔር ምን ግዴታ እንዳለብን የሚያስተምር ሲሆን ሁለተኛው በስድስቱ ትዕዛዛት በኩል ለሰዎች ምን ግዴታ እንዳለብን ያስተምረናል።

[1] ዘፀ. 34፡ 28፤ ዘዳ. 4፡ 13 [ 2] ማቴ. 22፡ 37—40

**94. እግዚአብሔር በመጀመሪያይቱ ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

በነብሴ መዳን ጥፋት ተወራርጀ ከሁሉም የጣኦት አምልኮ፣ ጥንቆላ፣ አስማተኞች፣ ቅዱሳንን እና ሌሎች ፍጥረታትን ከመማጸን እንድርቅ እና እነዚህ እንዳስወግድ እና ብቸኛ የሆነውን እውነተኛ አምላክ በተገቢው መንገድ እውቅና እንድሰጥ፣ በእርሱ ብቻ እንድናምን፣ በፍጹም ትህትና እና ትግስት በጎነትን ሁሉ ከእርሱ ብቻ እንድጠብቅ፣ በሙሉ ልቤ እንድወደው፣ እንድፈራው እና እንዳከብረው፣ በፈቃዱ ላይ ትንሹን ነገር ከማድረግ ይልቅ ፍጡራንን ሁሉ እንድክድ ይፈልጋል።

[1] 1 ቆሮ. 10፡ 7, 14 [2] ዘሌ. 19፡ 31፤ ዘዳ. 18፡ 10—12። [3] ማቴ. 4፡ 10፤ ራዕ. 19፡ 10፤ 22:8—9. [4] ዮሐ. 17፡ 3 [5] ኤር. 17፡ 5 [6] 1 ጴጥ. 5፡ 5—6. [7] ዕብ. 10፡ 36፤ ቈላ. 1፡ 10 ለ—11፤ ሮሜ. 5፡ 3—4; 1ቆሮ. 10፡ 10። [8] መዝ. 104፡ 27—30፤ ኢሳ. 45፡ 6—7፤ ያዕ. 1፡ 17 [9] ዘዳ. 6፡ 5 [10] ዘዳ. 6፡ 2፤ መዝ. 111፡ 10፤ ምሳሌ. 9፡ 10፤ ማቴ. 10:28 [11] ዘዳ. 10፡ 20 [12] ማቴ. 5፡ 29—30፤ 10:37; ሐዋ 5፡ 29

**95. ጣዖት አምልኮ ምንድን ነው?**

ጣዖት አምልኮ በቃሉ ውስጥ እራሱን በገለጠው አንድ እውነተኛ እግዚአብሔር ፋንታ ወይም ከእርሱ በተጨማሪ የምንተማመንበት ሌላ ነገር በውስጣችን መፀነስ ወይም መያዝ ነው።

[1] ኤፌ. 5፡ 5፤ ፊል. 3፡ 19፤ ኤፌ. 2፡ 12፤ ዮሐ. 2 ፡23፤ 2ዮሐ. 1 9፤ ዮሐ. 5፡ 23፤ *መዝ. 81፡8—9፤ *ማቴ. 6፡ 24፤ መዝ. 62፡ 5—7 * መዝ. 73፡ 25—26።

### የጌታ ቀን 35

**96. እግዚአብሔር በሁለተኛው ትእዛዝ ውስጥ ምን ይፈልጋል?**

በምንም መንገድ የእግዚአብሔርን መልክ እንዳንመስለው፣ በቃሉ እርሱ ካዘዘን በስተቀር በሌላ በምንም መንገድ እንዳናመለከው።

[1] ዘዳ. 4፡ 15—19፤ ኢሳ. 40፡ 18, 25። ሮሜ. 1፡ 22—24፤ ሐዋ 17፡ 29 [2] 1 ሳሙ. 15፡ 23፤ ዘዳ. 12፡ 30—32፤ ማቴ. 15፡ 9፤ *ዘዳ. 4፡ 23—24፤ *ዮሐ. 4፡ 24

**97. ምንም ዓይነት ምስል አንሰራም?**

እግዚአብሔር በምንም መንገድ ሊመሰል አይችልም፤ ፍጥረታቱ በእርግጥ በብዙ ነገር ሊመሰሉ ይችላሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን ለማምለክ ሆነ ለማገልገል የፍጥረታቱን ምስል ማበጀትን እና የተበጀውንም ምስል መያዝን ከልክሎኗል።

[1] ዘፀ. 23፡ 24—25፤ 34:13—14; ዘዳ. 7፡ 5፤ 12:3; 16:22; 2ነገ. 18፡ 4; *ዮሐ. 1፡ 18

**98. ይሁን እንጂ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ ሥዕሎች ለሰዎች የተዘጋጁ መጻሕፍት እንደሆኑ ተደርገው ሊታለፉ አይችሉም?**

በቃሉ ሕያው ስብከት እንጂ ሕዝቡ በዲዳ ጣዖታት እንዲማሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልሆነ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጥበበኞች ልንሆን አይገባንም።

[1] ኤር. 10፡ 8፤ ዕብ 2 18—19። [2] 2 ጴጥ. 1፡ 19; 2 ጢሞ. 3፡ 16—17፤ ሮሜ. 10፡ 17

### የጌታ ቀን 36

**99. በሦስተኛው ትእዛዝ ውስጥ ምን ያስፈልጋል?**

በመርገም፣ በሐሰት እና በአላስፈላጊ መሃላ የእግዚአብሔርን ስም እንዳናረክሰው እና አላግባብ እንዳንጠቀመው እንዲሁም እንዲህ ሲደረግ በዝምታ ባላማለፍ እና የዚህ ድርጊት ተባባሪ ባለመሆን የእንዲህ ያለው ህጢያት ተካፋይ እንዳንሆን ነው። ባጠቃላይ እግዚአብሔር በትክክል

# *የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)*

እኛ ዘንድ እንዲነገር እና እንዲመለክ እንዲሁም በድርጊታችን እና በቃላችን ይከብር ዘንድ ቅዱስ ስሙን በፍርሃት እና በታላቅ አክብሮት እንድንጠቀመው ነው።

[1] ዘሌ. 24፡ 10—16። [2] ዘሌ. 19፡ 12 [3] ማቴ. 5፡ 37፤ ያዕ. 5፡ 12 [4] ኢሳ. 45፡ 23 [5] ማቴ. 10፡ 32 [6] 1 ጢሞ. 2፡ 8 [7] ሮሜ. 2፡ 24፤ 1ጢሞ. 6፡ 1፤ ቆላ. 3፡ 16—17፤ *1 ጴጥ. 3፡ 15.

**100. የእግዚአብሔርን ስም በመሃላ እና በመራገም ማራከስ ይህንን ያክል ከባድ እንዲሁም ይህንን የሚያደርጉት እና ሲደረግም በዝምታ ሚመለከቱ ሰውች ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያመጣ ሃጢያት ነውን?**

አዎ፣ የእግዚአሔርን ስም ማራከስ ከሁሉም ሃጢያት በላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ ይቀሰቅሳል ስለዚህም ነው እግዚአብሔር ይህ ሃጢያት በሞት እንዲቀጣ ያዘዘው።

[1] ዘሌ. 5፡ 1 [2] ዘሌ. 24፡ 15—16; *ዘሌ. 19፡ 12፤ ምሳ። 29፡ 24- 25

### *የጌታ ቀን 37*

**101. ታዲያ በአክብሮት በእግዚአብሔር ስም አንምልም?**

ገዢዎች እና አለቆች ፊት ወይም በሌላ ሁኔታ አስፈላጊ ሲሆን መተማመንን እና እውነትን ለመጠበቅ እና ለማስረጽ እንምላለን ይህም ለእግዚአብሔር ክብርና ለወዳጆቻችን ጥቅም እንዲሆን ነው። እንደዚህ ያለው መሃላ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ እና ቅዱሳን በብሉይ እና አዲስ ኪዳን ይጠቀሙት የነበረ ነው።

[1] ዘዳ. 10፡ 20፤ ኢሳ. 48፡ 1፤ ዕብ. 6፡ 16። [2] ዘፍ. 21፡ 24፤ 31:53—54; ኢያሱ. 9፡ 15, 19፤ 1 ሳሙ. 24፡ 22፤ 1ነገ. 1፡ 29፤ ሮሜ. 1፡ 9

**102. በቅዱሳን ወይም በሌሎች ፍጥረታት መማል እንችል ይሆን?**

በፍጹም፣ እውነተኛ መሃላ ወደ እግዚአብሔር መጣራት ስለሆነ፣ እርሱ ብቻ ልብን ሚመረምር፣ ስለመሃላው በውነት ሚመሰክር እና በሃሰት ብንምል ሚቀጣን እርሱ ስለሆነ እንዲህ ባለ መሃላ ለእርሱ የሆነውን ክብር ለሌሎች ፍረታት አንሰጥም።

[1] 2 ቆሮ. 1፡ 23 [2] ማቴ. 5፡ 34—36፤ *ኤር. 5፡ 7፤ *ኢሳ. 65፡ 16

# የሃይድልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

### የጌታ ቀን 38

**103. እግዚአብሔር በአራተኛው ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

አንደኛ፡ እግዚአብሔር የወንጌል አገልግሎት እና ትምህርት ቤቶች እንዲቀጥሉ፣ በተለይም በእረፍት ቀን ቃሉን ለመማር፣ ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ፣ ከህዝቡ ጋር ወደ ጌታ ለመጣራት እና ክርስቲያናዊ በጎነትን ለማድረግ በትጋት ቤተክርስቲያ መገኘት።

ሁለተኛ፡ በሁሉም የሂወቴ ቀናቶች ከክፉ ስራ እናዳርፍ፣ እግዚአሔር በመንፈሱ በኔ እንዲሰራ እንድፈቅድ እና ዘላለማዊውን ሰንበት በዚህ ህይወት መለማመድ እንድጀምር ነው።

[1] ጢሞ. 1፡ 5፤ 1 ጢሞ. 3፡ 14—15፤ 4:13—14; 5:17; 1 ቆሮ. 9፡ 11, 13—14 [2] 2 ጢሞ. 2፡ 2, 15፤ መዝ. 40፡ 10—11፤ 68:26; ሐዋ 2፡ 42, 46 [3] 1 ቆሮ. 14፡ 19, 29, 31 [4] 1ቆሮ. 11፡ 33 [5] 1 ጢሞ. 2፡ 1— 2, 8—10፤ 1 ቆሮ. 14፡16። [6] 1ቆሮ. 16፡ 2 [7] ኢሳ. 66፡ 23፤ *ገላ. 6፡ 6፤ ሐዋ 20፡ 7፤ ዕብ. 4፡ 9—10።

### የጌታ ቀን 39

**104. እግዚአብሔር በአምስተኛው ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

ለአባቴ እና እናቴ እና በኔ ላይ ስልጣን ላላቸው ሁሉ አክብሮት፣ ፍቅርና ታማኝነት እንዳሳይ፣ ራሴን በተገቢው መታዘዝ ለነርሱ መካም ትዕዛዝ እና ወቀሳ እንዳስገዛ እንዲሁም እግዚአብሔር እኛን በነሱ እጄ ለመግዛት ፋቃዱ ስለሆነ ጉድለታቸውን በትዕግስት እንድንሸከም ነው።

[1] ኤፌ. 6፡ 22፤ ኤፌ. 6፡ 1—6፤ ቆላ. 3፡ 18, 20—24፤ ምሳሌ. 1፡ 8—9፤ 4:1; 15:20; 20:20; ዘጸ. 21፡ 17፤ ዘፍ. 9፡ 24—25። [2] ሮሜ. 13፡ 1፤ 1 ጴጥ. 2፡ 18; ሮሜ. 13፡ 2—7፤ ማቴ. 22፡ 21። [3] ኤፌ. 6፡ 4, 9፤ ቈላ. 3፡ 19, 21፤ *ምሳሌ 30፡ 17፤ *ዘዳ. 27፡ 16፤ *ዘዳ. 32፡ 24፤ *ምሳሌ 13፡ 24፤ *1 ጢሞ. 2፡ 1—2፤ *1 ጢሞ. 5፡ 17፤ ዕብ. 13፡ 17-18

### የጌታ ቀን 40

**105. እግዚአብሔር በስድተኛው ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

ወዳጆን በድርጊቴ ቀርቶ፣ በልቤ አሳብ፣ በቃሌ ወይም በአካላዊ ምልክት አላግባብ እንዳልቆጣ/እንዳልወቅስ፣ እንዳልጠላው፣ እናዳልሰድበው እንዲሁም እንዳልገድለው እናላስገድለው፣ ይልቁንስ የበቀልን ሃሳብ ሁሉ እንድተው ነው። ከዚህም በተጨማሪ እራሴን

እንዳልጎዳ፣ በፈቃዱ እራሴን አደጋ ላይ እንዳልጥል ነው። ስለዚህ ደግሞ ግድያን ለመከልከል ገዥው ሰይፍን ታጥቋል።

[1] ማቴ. 5፡ 21—22፤ 26:52; ዘፍ. 9፡ 6 [2] ኤፌ. 4፡ 26፤ ሮሜ. 1፡ 19፤ ማቴ. 5፡ 25፤ 18 35. [3] ማቴ. 4፡ 7፤ ሮሜ. 13፡ 14፤ ቈላ. 2፡ 23 [4] ዘፀ. 21፡ 14፤ *ማቴ. 18፡ 6—7

**106. ይሄኛው ትዕዛዝ ስለመግደል ብቻ ነው የሚናገረው?**

አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአሔር መግደልን በመከልከል የመግደል ስር የሆኑትን እንደ ክፉ ቅናት፣ ጥላቻ፣ ክፉ ቁጣ እና የበቀል ፍላጎትን አብዝቶ እንደሚጠላ እና እነዚህ ሁሉ በእግዚአሔር አይን ድብቅ ግድያወች እንደሆኑ ሊያስተምረን ነው።

[1] ሮሜ. 1፡ 28—32. [2] 1 ዮሐ. 2፡ 9—11 [3] ያዕ. 2፡ 13፤ ገላ. 5፡ 19—21። [4] 1 ዮሐ. 3፡ 15 *ያዕ. 3፡ 16፤ *1:19.

**107. የተፈለገው ግን ባልጀራችን እንዳንገድል ብቻ ነው?**

አይደለም፤ እግዚአብሔር ክፉ ቅናት፣ ጥላቻ፣ ክፉ ቁጣን በመኮነን ባልንጀራችን እንደራሳችን እንድንወድ፣ ትዕግስት፣ ሰላም፣ ፍጹም ትህትና፣ ምህረት እና በጎነትን እንድናሳየው እንዲሁም በተቻለን ሁሉ እርሱን ከጉዳት እንድጠብቀው ደግሞም ለጠላቶቻችን እንኳን መልካምን እንድናደርግ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

[1] ማቴ. 7፡ 12፤ 22፡ 39. [2] ኤፌ. 4፡ 2፤ ገላ. 6፡ 1—2፤ ሮሜ. 12፡ 18 [3] ማቴ. 5፡ 7፤ ሉቃ. 6፡ 36። [4] ሮሜ. 12፡ 10 [5] ዘፀ. 23፡ 5 [6] ማቴ. 5፡ 44—45፤ ሮሜ. 12፡ 20—21; ቆላ. 3፡ 12—14፤ *ማቴ. 5፡ 9

### *የጌታ ቀን 41*

**108. በሰባተኛው ትዕዛዝ ምን ያስተምረናል?**

ዘማዊነት በጠቅላላው በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ እንደሆነ እና በፍጹም ልባችን እንድንጠላው እንዲሁም በቅዱስ ጋብቻ ወይም በነጠላ ሂወት ተወስነን እና በተገቢው መኖር እንዳልብን ያስተምረናል።

[1] ዘሌ. 18፡ 27—28። [2] ይሁዳ 1፡ 22—23። [3] 1ተሰ. 4:3—5. [4] ዕብ. 13፡ 4፤ 1 ቆሮ. 7፡ 1—4

**109. እግዚአብሔር በዚህ ትዕዛዝ ከዝሙት ና መሰል ከባድ ሃጢያቶች በተጨማሪ ከልክሏል?**

ሰውነታችን እና ነብሳችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለሆኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁለቱንም ንጹህና ቅዱስ አድርገን እንድንጠብቃቸው ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር ዘማዊ ድርጊቶችን ሁሉ በሰውነት ማማለል ቢሆን፣ በቃላት፣ በሃሳብ፣ በፍላጎት እና በሌሎች መንገዶች እኛን ወደ ዝሙት ሚያነሳሱን ድርጊቶች ከልክሏል።

[1] ኤፌ. 5፡ 3—4፤ 1 ቆሮ. 6፡ 18—20። [2] ማቴ. 5፡ 27—30 [3] ኤፌ. 5፡ 18—19፤ 1ቆሮ. 15፡ 33

***የጌታ ቀን 42***

**110. እግዚአብሔር በስምንተኛው ትዕዛዝ ምንን ከለከለ?**

እግዚአብሔር በገዢዎች የሚያስቀጡትን እንደ ስርቆት እና ቀማኛነት ብቻ ሳይሆን የከለከለው፣ እግዚአብሔር ለባልጆራችን ጥቅም ስንል በማስገደድ ወይም በማታለል፣ ልከኛ ባልሆነ ክብደት፣ ርዝመት፣ ልኬታወች፣ እቃወች፣ ሳንቲሞች፣ አራጣ ወይም በማናቸውም እግዚአብሔር በከለከላቸው የሃጢያተኞች ማታለሎች ሚደረጉትን ነገሮች ሁሉ እንደ ስርቆት ያያቸዋል። እንዲሁም የሰውን ይዞታ መመኘት እና አላግባብ በማባከን የእግዚአብሔርን ስጦታ መጠቀምን ከልክሏል።

[1] 1 ቆሮ. 6፡ 10። [2] 1 ቆሮ. 5፡ 10። [3] ሉቃ. 3፡ 14; 1ተሰ. 4፡ 6. [4] ምሳሌ 11፡ 1፤ 16፡ 11. [5] ሕዝ. 45፡ 9—10። ዘዳ. 25፡ 13—15። [6] መዝ. 15፡ 5፤ ሉቃ. 6፡ 35። [7] 1 ቆሮ. 6፡ 10 [8] ምሳሌ. 5፡ 10; *1 ጢሞ. 6፡ 10፤ *ዮሐ. 6፡ 12

**111. እግዚአብሔር በዚህ ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

በምችለው ሁሉ የባልጆራየን ጥቅም እንዳስቀድም፣ ለሌች እንዲያደርጉልኝ ምፈልገውን ለሱ እናደርግ እና ድሆችን በሚያስፈልጋቸው እረዳ ዘንድ በታማኝነት እንድሰራ ነው።

[1] ማቴ. 7፡ 12 [2] ኤፌ. 4፡ 28፤ *ፊል. 2፡ 4፤ *ዘፍ. 3፡ 19፤ *1 ጢሞ. 6፡ 6—7

# የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( ኢ.ኤ.አ 1563)

## የጌታ ቀን 43

**112. ዘጠነኛው ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

በማንም ላይ በሃሰት እንዳልመሰክር፣ የማንንም ቃል እንዳላጣምም፣ ተናዳፊ እና ተሳዳቢ እንዳልሆን፣ ሳልሰማ እና በችኮላ እንዳልፈርድ ነገር ግን የእግዚአብሔርን የቁጣ መአት በማሰብ እንደ የሰይጣን ስራ ያሉ ዉሸት እና ማታለልን እንዳስወግድ እና በፍርድ እና በፍትህ እንዲሁም በማናቸውም ሌሎች ጉዳዮች እንድወድ፣ በሃቅ እንድናገር እና ስለ እውነት እንድመሰክር እንዲሁም በምችለው ሁሉ የባልጀራየን መልካም ስም እንድጠብቅ እና እንዳስቀድም ነው።

[1] ምሳሌ. 19፡ 5, 9 [2] መዝ. 15፡ 3 [3] ሮሜ. 1፡ 28—30. [4] ማቴ. 7 1—2 Lk. 6 37። [5] ዮሐ. 8 44 [6] ምሳሌ. 12፡ 22፤ 13፡ 5. [7] 1 ቆሮ. 13፡ 6፤ ኤፌ. 4፡ 25 [8] 1 ጴጥ. 4፡ 8; *ዮሐ. 7፡ 24, 51፤ *1 ጴጥ. 2፡ 21, 23; *ቆላ. 4 ፡6፤ *1 ጴጥ 3፡ 9

## የጌታ ቀን 44

**113. አስረኛው ትዕዛዝ ምን ይፈልጋል?**

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ የሚነሳ ምንም እንኳን ትንሽ ሚባል ዝንባሌ እና ሃሳብ ወደ ልባችን እንዳይገባ ነገር ግን በሙሉ ልባችን እና ያለ ማቋረጥ ሃጢያትን እንድንጠላ እና በቅድስና ደስ እንድንሰኝ ነው።

[1] ሮሜ. 7፡ 7—8፤ *ምሳሌ 4፡ 23፤ *ያዕ. 1፡ 14—15፤ *ማቴ. 15፡ 11, 19—20

**114. ወደ እግዚአብሔር የተመለሱት እነዚህን ትዕዛዛት በፍጹም ሊጠብቁ ይቻላቸዋል?**

በፍጹም፣ ከሰዎች ሁሉ ቅዱስ የተባሉት እንኳን አይችሉም። በዚህ ህይወት እያለን እንደዚህ ያለው ፍጹም መታዘዝ ትንሽ ጅማሬ ብቻ ይኖረናል፣ ነገር ግን በቅን አላማ በአንዳንዶች ብቻ ሳይሆን በሁሉም የእግዚአብሔር ትዕዛዛት መሰረት መኖር ይጀምራሉ።

[1] 1 ዮሐ. 1፡ 8—10፤ ሮሜ. 7፡ 14—15፤ መክ. 7፡ 20 [2] ሮሜ. 7፡ 22፤ ያዕ. 2፡ 10—11፤ *ኢዮብ 9፡ 2—3፤ *መዝ. 19፡ 13

**115. በዚህ ህይወት ማንም ሊጠብቃቸው ካልቻለ ታዲያ ለምን እግዚአብሔር አስርቱን ትዕዛዛት በኛ ላይ አጥብቆ አዘዘን?**

በመጀመሪያ፣ በሕይወት እስካለን ድረስ የኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን ለማወቅ የበለጠ እንድንማር፣ እናም በክርስቶስ የኃጢአትን ስርየት እና ጽድቅን በትጋት እንድንሻ። ሁለተኛ፣ ከዚህ ሕይወት በኋላ የፍጽምናን ግብ እስክንደርስ ድረስ፣ በእግዚአብሔር መልክ እየታደስን ሳናቋርጥ እግዚአብሔርን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በትጋት እንድለምን ነው።

[1] 1 ዮሐ. 1፡ 9; መዝ. 32፡ 5 [2] ሮሜ. 7፡ 24-25 [3] 1 ቆሮ. 9: 24—25፤ ፊል. 3: 12—14፤ *ማቴ. 5: 6፤ *መዝ. 51: 12

## ጸሎት

### የጌታ ቀን 45

**116. ጸሎት ለክርስቲያኖች አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው የምስጋና ዋና አካል ስለሆነ፣ እና እግዚአብሔር ፀጋውንና መንፈሱን ቅዱሱን በትጋትና ያለማቋረጥ ለሚለምኑት ብቻ ስለሚሰጥ እና ስለሰጠን ጸጋ እና መንፈስ ቅዱስ ለማመስገን ነው።

[1] መዝ. 50: 14—15። [2] ማቴ. 7: 7—8፤ ሉቃ. 11፡ 9—10, 13፤ ማቴ. 13፡ 12፤ *ኤፌ. 6፡ 18

**117. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ካለው እና ከሚሰማው ጸሎት ውስጥ ምንድን ነው?**

በመጀመሪያ፣ እንድንለምነው ያዘዘንን ሁሉ በቃሉ ራሱን ወደ ገለጠው ወደ አንዱ እውነተኛ አምላክ በፍጹም ልባችን እንድንጣራ ሁለተኛ፣ የሚያስፈልገንን እና ችግራችንን ጠንቅቀን በማወቅ በመለኮታዊ ግርማው ፊት ራሳችንን እንድናዋርድ ሦስተኛው፡ በቃሉ ተስፋ እንደ ሰጠን የተገባን ባንሆንም እርሱ ስለ ጌታችን ክርስቶስ ሲል በእውነት የእኛን ቃል እንደሚሰማ እርግጠኞች እንድንሆን ነው።

[1] ዮሐ. 4፡ 22—24 [2] ሮሜ. 8፡ 26፤ 1 ዮሐ. 5፡ 14። [3] መዝ. 27፡ 8 [4] 2 ዜና 20፡ 12 [5] መዝ. 2፡ 10፤ 34:18; ኢሳ. 66፡ 2። [6] ሮሜ. 10፡ 14፤ ያዕ. 1፡ 6 [7] ዮሐ. 14፡ 13—16፤ ዳን. 9፡ 17—18 [8] ማቴ. 7፡ 8፤ መዝ. 143፡ 1፤ *ሉቃ. 18: 13

**118. እግዚአብሐር እርሱን እንድንለምነው ያዘዘን ምንድን ነው?**

ጌታችን ክርስቶስ እኛን ባስተማረበት በትምህርቱ እንዳካተተው፣ ለነብስና ለስጋችን የሚያፈልገንን ነገር ነው።

[1] ያዕ. 1: 17 ማቴ. 6: 33 *1 ጴጥ. 5: 7. *ፊል. 4: 6

**119. የጌታ ጸሎት ምንድን ነው?**

እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

[1] ማቴ. 6: 9—13፤ ሉቃ. 11፡ 2—4.

*የጌታ ቀን 33*

**120. ክርስቶስ ለምን እግዚአብሔርን አባታችን ብለን እንድንጠራው አዘዘን?**

በጸሎታችን መጀመሪያ ላይ በውስጣችን እንድንነቃ እንደ ሕፃን እግዚአብሔርን ማክበር እና መታመን የጸሎታችን መሠረት እንዲሆን ማለትም እግዚአብሔር በክርስቶስ አባታችን እንደ ሆነ እና ወላጆቻችን ምድራዊውን ነገር እንደማይከለክሉን ይልቁንም እርሱ በእምነት የጠየቅነውን እንደማይከለክለን ነው።

[1] ማቴ. 7፡ 9—11፤ ሉቃ. 11፡ 11—13; *1 ጴጥ. 1፡ 17; *ኢሳ. 63፡ 16

**121. "በሰማይ" ተብሎ የተጨመረው ለምንድን ነው?**

ስለ እግዚአብሔር ሰማያዊ ግርማ ምንም አይነት ምድራዊ ሀሳብ እንዳይኖረን እና ከኃይሉ ለሥጋ እና ለነፍስ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ እንድንጠብቅ ነው።

[1] ኤር. 23፡ 23—24፤ ሐዋ 17፡ 24-25, 27 [2] ሮሜ. 10: 12; ነገ. 8 28; *መዝ. 115: 3

# የሃይድልበርግ ካቴኪዝም ( ኢ.ኤ.አ 1563)

## የጌታ ቀን 47

**122. የመጀመሪያው አቤቱታ ምንድን ነው?**

"ስምህ ይቀደስ" ይኸውም በመጀመሪያ አንተን እንድናውቅህ ስጠን፤ ኃይልህ፣ ቸርነትህ፣ ፍርድህ፣ ምሕረትህና እውነትህ በሚበሩበት ሥራህ ሁሉ ልንቀድስ፣ እንድናከብርህና እንድናመሰግንህ ነው። ከዚህም በላይ ህይወታችንን፣ ሀሳባችንን፣ ቃሎቻችንን፣ እና ተግባራችንን እንታዘዝህ ዘንድ፣ ስምህ እንዳይሰደብ፣ ነገር ግን በእኛ ምክንያት እንዲከበር እና እንዲመሰገን።

[1] ዮሐ. 17: 3፤ ማቴ. 16: 17፤ ያዕ. 1: 5፤ መዝ. 119: 105። [2] መዝ. 119: 137፤ ሮሜ. 11: 33—36። [3] መዝ. 71: 8፤ *መዝ. 100: 3—4፤ *መዝ. 92: 1—2፤ *ኤፌ. 1: 16—17፤ *መዝ. 71: 16

## የጌታ ቀን 48

**123. ሁለተኛው አቤቱታ ምንድን ነው?**

መንግሥትህ ትምጣ; ማለትም፣ ስለዚህ በቃልህ እና በመንፈስህ ግዛን፣ ሁል ጊዜ ራሳችንን የበለጠ ለአንተ እናስገዛለን፡ ቤተክርስቲያንህን ጠብቅ እና አሳድግ። የመንግሥትህ ሙላት እስኪመጣ ድረስ የዲያብሎስን ሥራ፣ በአንተ ላይ ራሱን ከፍ የሚያደርግን ኃይል ሁሉ፣ በቅዱስ ቃልህ ላይ የተሠራችውን ክፉ አሳብ ሁሉ አጥፋ፣ በዚያን ጊዜ አንተ ሁሉ በሁሉ ትሆናለህ።

[1] መዝ. 119: 5፤ 143: 10. [2] መዝ. 51: 18፤ 122:6—7. [3] 1 ዮሐ. 3: 8፤ ሮሜ. 16: 20። [4] ራዕ. 22: 17, 20፤ ሮሜ. 8: 22—23. [5] 1 ቆሮ. 15: 28፤ *መዝ. 102: 12—13፤ ዕብ. 12: 28፤ *ራዕ. 11፡15፤ *1ቆሮ. 15፡ 24

## የጌታ ቀን 49

**124. ሦስተኛው አቤቱታ ምንድን ነው?**

"ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን።" ማለትም፣ እኛ እና ሰዎች ሁሉ የራሳችንን ፈቃድ እንድንክድ እና ያለ ጥርጥር መልካም ብቻ የሆነውን ትዕዛዝህን እንድንጠብቅ

ነው:: ይህውም መላእክት በሰማይ እንደሚያደርጉት ሁሉ ሁሉም ሰው በፈቃዱና በታማኝነት ሥራውንና ጥሪውን እንዲፈጽም ነው::

[1] ማቴ. 16፡ 24 [2] ሉቃ. 22፡ 42; ቲቶ. 2፡ 12:: [3] 1 ቆሮ. 7፡ 24 [4] መዝ. 103፡ 20 21፤ሮሜ. 12፡ 2፤ ዕብ. 13፡ 21

### የጌታ ቀን 50

**125. አራተኛው አቤቱታ ምንድን ነው?**

"የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" ማለትም ለሥጋችን የሚያስፈልገንን ሁሉ በማሟላት ደስ እንድሰኝ፣ በዚህም የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ አንተ ብቻ እንደሆንክ እውቅና እንድንሰጥ፣ እናም የእኛ ጥንቃቄም ሆነ ድካማችን እንዲሁም ያንተ ስጦታዎች ያለአንተ በረከት ለኛ ምንም እንድማይጠቅሙን እውቅና እንድንሰጥ፣ ስለዚህም መደገፋችንን ሁሉ ከፍጡራን አንስተን ባንተ ላይ ብቻ እንድናስቀምጥ ነው::

[1] መዝ. 104 27—28፤ 145:15—16; ማቴ. 6 25—26:: [2] የሐዋርያት ሥራ 14 17፤ 17:27—28. [3] 1 ቆሮ. 15 58፤ ዘዳ. 8 3፤ መዝ. 37 3—7, 16—17:: [4] መዝ. 55 22፤ 62:10; *መዝ. 127 1—2፤ *ኤር. 17 5, 7፤ *መዝ. 146 2—3::

### የጌታ ቀን 51

**126. አምስተኛው አቤቱታ ምንድን ነው?**

"የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን::" ይኸውም ስለ ክርስቶስ ደም ደስ ይበለን፤ ኀጢአተኞች ሆነን እንደ መተላለፋችን ወይም ሁልጊዜም በእኛ ላይ የሚጣበቅን ክፉ ነገር በእኛ ላይ እንዳልቆጠረ ሁሉ እኛም በጸጋው ምስክር በእኛ ዘንድ እንደተቀበልን ጎረቤታችንን በሙሉ ልባችንን ይቅር እንድንል የቀረበ አላማ ነው::

[1] መዝ. 51፡1—4፤ 143:2; 1 ዮሐ. 2፡ 1—2 [2] ማቴ. 6፡ 14—15፤ መዝ. 51፡ 5—7፤ ኤፌ. 1፡ 7

# *የሃይደልበርግ ካቲኪዝም( እ.ኤ.አ 1563)*

### *የጌታ ቀን 52*

**127. ስድስተኛው አቤቱታ ምንድን ነው?**

"ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን" ማለትም በራሳችን በጣም ደካሞች ስለሆንን ለአንድ አፍታ መቆም አንችልም.እኔ እና ከዚህ በተጨማሪ ገዳይ ጠላቶቻችን ዲያብሎስ፣ አለም፣ ሥጋችንም ሳያቋርጡ ስለሚያንገላቱን በመንፈስ ቅዱስህ ኃይል እኛን በመጠበቅ እና በማበርታት ደስ ይበልህ፤ ይሄውም በእነርሱ ላይ ጸንተን እንድንቆምና በዚህ መንፈሳዊ ጦርነት አሸንፈን፤ በመጨረሻም ፍጹም ድል የእኛ እስክሆን ድረስ ነው።

**128. ይህን ጸሎት እንዴት ነው ምንዘጋው?**

*መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለም።" ይህ ሁሉ ከአንተ እንለምናለን፤ ምክንያቱም ንጉሣችን እንደመሆናችን መጠን በነገር ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለህ አንተ መልካሙን ሁሉ ልትሰጠን ትወዳለህና ትችላለህ። በዚህም የእኛ ሳይሆን፤ ቅዱስ ስምህ ግን ለዘላለም ይከበር።*

[1] ዮሐ. 15፡ 5፤ መዝ. 103፡ 14—16። [2] 1ጴጥ. 5፡ 8—9፤ ኤፌ. 6፡ 12—13። [3] ዮሐ. 15፡ 19 [4] ሮሜ. 7፡ 23፤ ገላ. 5፡ 17 [5] ማቴ. 26፡ 41፤ መ. 13 33። [6] 1ተሰ. 3:13; 5:23—24; *2 ቆሮ. 12፡ 7

**129. አሜን የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?**

"አሜን" ማለት፡ በእውነትና በእርግጥ ይሆናል ማለት ነው። በልቤ ከሚሰማኝ በላይ ጸሎቴ በእውነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰምቷልና እነዚህን ነገሮች ከእርሱ እንድፈልግ ነው።

[1] 2 ቆሮ. 1፡ 20፤ 2 ጢሞ. 2፡ 13፤ *መዝ. 145፡ 18—19

"እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"

**ኤፌ 3፡ 20-21**